# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 049 ጥቅምት 19 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ከ610 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ርዳታ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ተከፋፍሏል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት 15 ቀናት በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች ከ610 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ርዳታ መከፋፈሉን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን ገለጸ። ዜጎች ለወገን አለኝታነት እና የመደጋገፍ ባህልን ማጠናከር ይገባቸዋል ተብሏል።

የኮሚሽኑ ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አታለለ አቡሃይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው አራት ሚሊዮን ለሚደርሱ ዜጎች ከ610 ሺህ ኩንታል በላይ በቆሎ፣ ዱቄት፣ ሩዝ እና መሰል ምግቦች ርዳታ ተከፋፍሏል።

በተጨማሪም ለርዳታ ፈላጊዎች 54 ሺህ ኩንታል አልሚ ምግቦች፤ ለእናቶች፣ ለሕጻናት እና ለነፍሰ ጡሮች መንግሥት ድጋፍ አድርጓል። አንድ ሚሊዮን ሊትር ዘይትም እንደደረሰ ተነግሯል።

ከተለያዩ ተቋማት በተገኘው ፈንድ መሠረት አንድ ነጥብ

ከ610 ሺህ ኩንታል... ወደ ገጽ6 ዞሯል

# "ኢትዮጵያ በበጋ መስኖ፣ በሌማት ትሩፋትና በአረንጓዴ ልማት ሥራዎች አመርቂ ውጤት እያስመዘገበች ነው"

- የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር)



**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በበጋ መስኖ፣ በሌማት ትሩፋትና በሌሎች የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች አመርቂ ውጤት እያስመዘገበች ነው ሲሉ የግብርና ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) ተናገሩ።

የግብርና ሚኒስቴር ለክልሎች የመኪናና የሞተር ብስክሌቶች፤ እንዲሁም ለመልካሳ ግብርና ምርምር ማዕከል የቤተ ሙከራ መሣሪያዎች ድጋፍ በትናንትናው ዕለት አድርጓል።

በርክክብ ሥነሥርዓቱ ላይ የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ግርማ አመንቴ (ዶ/ር) እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በበጋ መስኖ፣ በሌማት ትሩፋትና በሌሎች የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች አመርቂ ውጤት እያስመዘገበች ነው። ለዚህ ደግሞ የሁሉም የባለድርሻ አካላት ትብብርና ከአጋዥ ድርጅቶች ጋር በቅንጅት መሥራቱ ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

በመስኖ፣ በበልግ፣ በመኸር ሰፊ እቅዶች ተይዘው

"ኢትዮጵያ በበጋ... ወደ ገጽ6 ዞሯል












# በበጀት ዓመቱ ከሆልቲካልቸር ዘርፍ 720 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዷል

- በሩብ ዓመቱ ከ129 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት ከሆለቲካልቸር ዘርፍ 720 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ለማግኘት መታቀዱን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ። በሩብ ዓመቱ ከሆለቲካልቸር ዘርፍ ከ129 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱ ተጠቁሟል።

በበጀት ዓመቱ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






# ቴክኒክና ሙያ ተቋማት 600 ሺህ ተማሪዎችን ለመቀበል ተዘጋጅተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- 12ኛ ክፍል ካጠናቀቁት ተማሪዎች ውስጥ በዘንድሮው ዓመት በቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚገቡ 600 ሺህ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅት መደረጉን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በሚኒስቴሩ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ እንደ ሀገር ከ700 በላይ የመንግሥትና ከ900 በላይ የግል የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት አሉ። እነዚህ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት 600 ሺህ ተማሪዎችን ለመቀበል ዝግጅት አድርገዋል።

የትምህርት ተቋማቱ ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ

ቴክኒክና ሙያ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ተሻለ በሬቻ (ዶ/ር)

# በመዲናዋ ከደረቅ ቆሻሻ አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል

## - በሩብ ዓመቱ 381 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ደረቅ ቆሻሻን መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ለማግኘት ማቀዱን የአዲስ አበባ ከተማ ፅዳት አስተዳደር ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ በሩብ ዓመቱ 381 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ተገኝቷል፡፡

በኤጀንሲው የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት አስተዳደር ዳይሬክተር ወይዘሮ ባዩሽ ታደሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት 87 ሺህ ቶን ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሠራ ነው፡፡ እንዲሁም ከደረቅ ቆሻሻው ሦስት ሺህ ቶን ኮምፖስት በማምረትና በመሸጥ አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር ለማግኘት ታቅዷል፡፡

እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ፤ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት 21 ሺህ 604 ቶን ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና መልሶ ጥቅም ላይ በማዋል እንዲሁም ከደረቅ ቆሻሻ 680 ቶን ኮምፖስት በማምረትና በመሸጥ 381 ሚሊዮን 227 ሺህ በላይ ብር በዘርፉ ከተሰማሩ ማህበራት ገቢ ተገኝቷል፡፡

ገቢው ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ለመልሶ መጠቀም እና ኡደት የዋለ ደረቅ ቆሻሻ አንድ ሺህ 698 ቶን መጨመሩን አውስተው፤ ለዚህም



ወይዘሮ ባዩሽ ታደሰ

ማህበራት አቅማቸውን በማጠናከር ለሥራው ትኩረት ሰጥተው በመሥራታቸው የተገኘ ውጤት መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአራዳ፣ ልደታና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ የተሰማሩ ማህበራት በመሥሪያ ቦታ ዕጥረት እንደሚቸገሩ ገልጸው፤ ኤጀንሲው ከመሬት ማኔጅመንት ጋር በመቀናጀት ችግሩን ለመቅረፍ እየተሠራ መሆኑን ዳይሬክተሯ አስረድተዋል፡፡

ዳይሬክተሯ አክለውም በኮምፖስቱ ዘርፍ ላይ የገበያ ትስስር ከመፍጠር አንጻር ውስንነቶች አሉ ያሉ ሲሆን፤ ችግሮቹን ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር ለመፍታት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ቆሻሻ በሥርዓት ከልተያዘና መልሶ ጥቅም ላይ ካልዋለ በሀገር ደረጃ የሚፈጥረው ዘርፈ ብዙ ጫና ከፍተኛ መሆኑን ዳይሬክተሯ ጠቁመዋል፡፡

ኤጀንሲው በዘርፉ ለተሰማሩ ማህበራት የአቅም ግንባታ ሥልጠና መስጠትን ጨምሮ የቆሻሻ አሰባሰቡን ዘመናዊ መንገድን የተከተለ እንዲሆን ለማድረግ አቅጣጫ አስቀምጦ እየሠራ መሆኑን ዳይሬክተሯ አስረድተዋል፡፡

ቆሻሻን ወደ ሀብት ለመለወጥ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንደ ሀገር የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ ህብረተሰቡ ኃላፊነቱን ሊወጣና ለዘርፉ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

# ክልሉ ከማዕድንና ኢነርጂ 40 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት እየሠራ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት ከማዕድንና ኢነርጂ ዘርፍ 40 ሚሊዮን ብር ገቢ ለማግኘት እየሠራ መሆኑን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ አስታወቀ፡፡ በዘርፉ ከስድስት ሺህ 800 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል።

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ገብረማርያም ሰጠኝ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ ያለውን የማዕድን ሀብት በመጠቀም የተሻለ ገቢ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ባለፈው ዓመት ከዘርፉ ከ39 ሚሊዮን በላይ ብር ገቢ ማግኘት ተችሏል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመትም 40 ሚሊዮን ብር ለማግኘት ውጥን ተይዟል ብለዋል።

ኤጀንሲው የማዕድን ሀብት ጥናት፣ አስተዳደርና የአማራጭ ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ማስፋፋት ዘርፎች ላይ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ የጠቆሙት አቶ ገብረማርያም፤ የድንጋይ ከሰል፣ የኮንስትራክሽን ማዕድናትና ለልዩ አነስተኛ ወርቅ አምራች ማህበራት ፍቃድ ተሰጥቶ በዘርፉ የሥራ ዕድል መፈጠሩን አመላክተዋል።

በዘርፉ ባለፈው በጀት ዓመት ከአራት ሺህ 500 ለሚልቁ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል፤ በተያዘው በጀት ዓመት ከስድስት ሺህ 800 በላይ ለሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር እየተሠራበት ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ ገብረማርያም ገለጻ፤ በክልሉ በወርቅ ምርትና ንግድ ዘርፍ የተሰማሩ 21 ማህበራት በሥራ ላይ ይገኛሉ፡፡

በኮንታና ዳውሮ ዞኖች የድንጋይ ከሰል የቅኝት፣ የምርመራና የማምረት ፈቃድ አሰጣጡ ለጊዜው እንዲቋረጥ መደረጉ በታቀደው ልክ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ተግዳሮት እንደሆነ ገልጸው፤ በቀጣይ ችግሩ ሲፈታ እቅዱን ማሳካት የሚቻልበት ሁኔታ እንደሚኖር አብራርተዋል፡፡

በማዕድን ዘርፍ በመሰማራት ወደሥራው ለመግባት ፍላጎት ያላቸው ዜጎች ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ያነሱት አቶ ገብረማርያም፤ አሁን ላይ 120 የሚጠጉ ማህበራት ጥያቄ ያቀረቡ በመሆኑ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስትራቴጂ እየተዘጋጀ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡


የማህበራቱን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ከድንጋይ ከሰል ውጪ ሌሎች ማዕድናት በክልሉ የሚገኙ በመሆኑ በሌሎች ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ችግሩን ለመፍታ መታሰቡን አመላክተዋል።

በክልሉ በድንጋይ ከሰል የቅኝት ፍቃድ ጠይቀው የነበሩ 74 ማህበራት ሲሆኑ በአጠቃላይ 13 የሚሆኑ ማህበራት የማምረት ፍቃድ የወሰዱ ቢሆንም ሰባቱ ብቻ በማምረት ሂደት ላይ ይገኛሉ ብለዋል።

ከዳውሮና ኮንታ በተጨማሪ በካፋ፣ በማጂ፣ በምዕራብ ኦሞ ላይ ሥራዎች የተጀመሩ ሲሆን፤ በቀጣይም በሸካና በቤንች ሸኮ አካባቢዎች ላይም ቅኝቶች እየተደረጉ የሚሠራበት ሁኔታ እንደሚኖር ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

የድንጋይ ከሰል በብዛት የሚያስፈልገው ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች በመሆኑ በሀገር ውስጥ መመረቱ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሬ በማትረፍ ረገድ ሚናው የጎላ መሆኑን ጠቁመው፤ አቅም ያላቸው ባለሀብቶች በስፋት በዘርፉ ላይ እንዲሰማሩ ለማድረግ እየተሠራበት መሆኑን ተናግረዋል።

በወርቅ ማዕድን ላይ ሕገ-ወጥ አሰራሮች በመንሰራፋታቸው ምርቱ ቢኖርም በሕገወጥ ገበያ የሚሸጥ በመሆኑ ተገቢውን ጥቅም ማግኘት አልተቻለም ያሉት አቶ ገብረማርያም፤ ሁሉም ህብረተሰብ ሕገወጥ አሠራሩ ያለውን ጉዳት ተመልክቶ ለጸጥታና ተቆጣጣሪ አካላት አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።



አቶ ሰለሞን ስለሺ

# ከ460 በላይ ሃሰተኛ ሰነዶች ተያዙ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- 462 ሃሰተኛ የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያና የጋብቻ ማስረጃ መያዙን የፌዴራል ሰነዶች ማረጋገጫ እና ምዝገባ አገልግሎት አስታወቀ።

የአገልግሎቱ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሰለሞን ስለሺ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አገልግሎቱ በተያዘው ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ከ246 ሺህ በላይ ልዩ ልዩ የውል ሰነዶችን ማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ ውስጥ 462 የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያና የጋብቻ ማስረጃዎች ሃሰተኛ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ከተያዙት ሃሰተኛ ማስረጃዎች 367 የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያዎች፣ 69 የጋብቻ ማስረጃዎች እና 26 ልዩ ልዩ የውል ሰነዶች መሆናቸውን የጠቀሱት አቶ ሰለሞን፤ አገልግሎቱ ከፍትህ ሥርዓቱ ጋር በተያያዘ ወንጀሎችን ለመከላከል በቀን ከስድስት ሺህ በላይ ሰነዶች ሕጋዊነታቸው ይረጋገጣል ብለዋል።

በአገልግሎቱ የነበሩ አሠራሮቹ የሚያሰለቹ፣ ለወንጀሎች የተጋለጡ እና የሰነዶች ጥራት ችግር የነበረባቸው እንደነበር ጠቁመው፤ ይህም ሀሰተኛ ሰነዶች እንዲፈጠሩ በማድረግ ሀገር በማጭበርበር ወንጀል ከፍተኛ ሀብት እንድታጣ ሲያደርጋት መቆየቱን ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሰለሞን ገለፃ፤ አሁን ላይ አሠራሩ በዲጅታል እየታገዘ በመሆኑ ችግሩን በተወሰነ ደረጃ ትርጉም ባለው መልኩ መቀነስ ተችሏል፡፡ ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት 27 ከሚሆኑ ባንኮች እና ከመንግሥት ተቋማት ጋር አገልግሎቱ በጋራ እየተሠራ ይገኛል።

አገልግሎቱ በአሁኑ ወቅት ሀሰተኛ ሰነድን በመጠቀም የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ከባንኮች እና ከተለያዩ አካላት ጋር በቅንጅት እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ የሰነድ ጉዳይ ትልቅ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ ሰነዶች በአግባቡ ሊያዙና ሊፈተሹ ይገባል። ይህም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል።

በቀጣይም ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ትስስር በመፍጠር ችግሩን ለመቅረፍ እንደሚሠራም ገልጸዋል።

በ2015 በጀት ዓመት ለአገልግሎት ቀርበው የተያዙና አገልግሎት እንዳይሰጥባቸው የተደረጉ የማንነት ማረጋገጫ መታወቂያ አንድ ሺህ 509፣ የጋብቻ ማስረጃዎች 178 እና ሌሎች ልዩ ልዩ ሰነዶች 36 በድምሩ አንድ ሺህ 723 ሃሰተኛ ሰነዶች መያዛቸውን ተናግረዋል።

አገልግሎቱ አምና ለአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ለሚሆኑ ተገልጋዮች አገልግሎት መስጠት መቻሉን የጽህፈት ቤት ኃላፊው አቶ ሰለሞን ስለሺ ገልጸዋል።

# በክልሉ ከ17 ሺህ 300 በላይ የሆኑ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ያስፈልጋቸዋል

## • በሩብ ዓመቱ 543 ዜጎች አገልግሎቱን አግኝተዋል

**ቃልኪዳን አሳዬ**



አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከ17 ሺህ 300 በላይ የሆኑ ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ። በሩብ ዓመቱ ለ543 ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ማድረግ መቻሉ ተገልጸዋል፡፡

በቢሮው ትኩረት የሚሹ ሀሩራማ በሽታዎች ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ኃይለየሱስ ተረፈ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ከዓይን ቆብ መቀልበስ ጋር ተያይዞ ለዓይነ ስውርነት በሚያጋልጠው የትራኮማ በሽታ ተጠቅተው የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልጋቸው 17 ሺህ 326 ዜጎች ይገኛሉ፡፡

በበጀት ዓመቱ እየተከናወኑ ካሉ ተግባራት መካከል በሽታው በስፋት በሚገኝባቸው ወረዳዎች ላይ መድኃኒት የማደል ሥራ እየተሠራ ነው፤ በዚህም በሩብ ዓመቱ ለ72 ሺህ 841 ዜጎች የመድኃኒት እደላ ተደርጎላቸዋል።

የተጠቂዎች ቁጥር ከዚህ በላይ በመሆኑ የመድኃኒት እጥረት እንዳለ የገለጹት አቶ ኃይለየሱስ፤ በተቻለ መጠን ለማዳረስ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በክልሉ በሚገኙ በጉራጌ፣ በስልጤ፣ በሀዲያ፣ በከንባታ ጠንባሮና በሃላባ ዞኖች ላይ ጫናው ከፍተኛ ሲሆን የዓለም ጤና ድርጅት በሚያስቀምጠው ቅድመ ሁኔታ መሠረት የስርጭት መጠናቸው ከአምስት በመቶ በታች የሆነባቸው ወረዳዎች ከትራኮማ ነጻ እንደሆኑ ታስቦ የመድኃኒት እደላ እንደሚቋረጥ ጠቁመዋል፡፡

እንዲሁም ትራኮማ በባክቴሪያ አማካኝነት የሚመጣ በሽታ እንደመሆኑ መጠን የፊትና የአካባቢ ንፅህና መጠበቅ አስፈላጊ በመሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ላይ በስፋት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ኃይለየሱስ ገለጻ፤ ከመድኃኒት እደላው በተጨማሪ የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ሙያ የሠለጠኑ ባለሙያዎች በክልሉ ተሰማርተው ሰፊ ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ፤ በዚህም በሩብ ዓመቱ ለ543 ዜጎች የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና ማድረግ ተችሏል፡፡

የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የአዝመራ ወቅት በመሆኑ የበሽታው ተጠቂ የሆኑ ዜጎች ቀዶ ህክምና ለማድረግ ፍቃደኛ አለመሆን ሥራውን ለማከናወን አዳጋች አድርጎት ነበር ያሉት አቶ ኃይለየሱስ፤ በሽታውን ለመከላከል ብዛት ያላቸው ወረዳዎች የመድኃኒት እደላና የዓይን ቆብ ቀዶ ጥገና እንደሚያስፈልጋቸው አንስተዋል፡፡

ትራኮማ በዋናነት የሚያጠቃው ህጻናትን በመሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትራኮማ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተማሪዎች የፊት ንፅህናቸውን እንዲጠብቁ ማስተማር፣ በመኖሪያም ሆነ በትምህርት ቤቶች በመጠነኛ ብልሽት የቆሙ የውሃ አቅርቦት መስመሮችን በመጠገንና በተወሰኑ ወረዳዎች ላይ የዝናብ ውሃን በመያዝ አገልግሎት ላይ ለማዋል ከአጋር አካላት ጋር እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች እንዳሉ አቶ ኃይለየሱስ ጠቁመዋል፡፡

የጤና ኤክስቴንሽንና የወሽ ፕሮግራሞችን በመጠቀም የማህበረሰብ አቀፍ ውይይቶችን በማከናወን ነጻ ቀበሌዎችን የመፍጠር ሥራው በቅንጅት ይሠራል ያሉት አቶ ኃይለየሱስ፤ ክልሉ ገና በመዋቀር ላይ ያለ በመሆኑ የሰው ኃይል ቅጥር በማከናወንና የሙያ ሥልጠናዎችን በመስጠት የተሻለ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡



አስራት ጤራ (ዶ/ር)

# በበጀት ዓመቱ 38 ሺህ ቶን ስጋ ለውጭ ገበያ ይላካል

**አመስወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ዓመት 38 ሺህ ቶን ስጋ ለውጭ ገበያ በመላክ ከ140 ሚሊዮን በላይ ዶላር ለማግኘት መታቀዱን የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡

የእንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳሬክተር አስራት ጤራ (ዶክተር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮው በጀት ዓመት 38 ቶን ስጋ ለውጭ ገበያ በማቅረብ 140 ነጥብ 12 የአሜሪካን ዶላር ለማግኘት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ዶክተር አስራት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ለ14 ዓመታት ከዘርፉ ንግድ አንድ ነጥብ አንድ ቢሊዮን ዶላር ብቻ ነው ያገኘችው። በመሆኑም በዘንድሮው ዓመት በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍ 140 ነጥብ 12 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት እየተሠራ ነው፡፡

በሀገሪቱ ስጋን አቀነባብረው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ 12 ህጋዊ ቄራዎች መኖራቸውን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ እነዚህም ቄራዎች መስራት ከሚችሉት አቅም በታች እየሠሩ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ዶክተር አስራት ገለጻ፤ ቄራዎቹ በዓመት የማቀነባበር አቅማቸው 120 ሺህ ቶን ስጋ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት 20 ሺህ ቶን ስጋ እያቀነባበሩ ነው የሚገኙት።

ለዚህም ዋናው ምክንያት የህገወጥ ንግድ መስፋፋት መሆኑን ያነሱት ኃላፊው፤ በሀገሪቱ ድንበር አካባቢ በሚገኙ ቦታዎች በስፋት እንስሳት የሚረቡ ቢሆንም ወደጎረቤት ሀገራት በኮትሮባንድ እንደሚሸጡ ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም እንንስሳት ለሽያጭ በሚጓጓዙበት ወቅት በየአካባቢው የኬላዎች መበራከትና ከፍተኛ ቀረጥ ነጋዴዎች መጠየቃቸው ለሥራው ተግዳሮት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ችግሩን በመቅረፍ የወጪ ንግዱን ለማሳደግ እንስሳት በብዛት ያሉባቸውን አካባቢዎች በጥናት በመለየት ከገበያ ጋር የማስተሳሰር ሥራ እየተሠራ ይገኛል፡፡

ኮንትሮባንድን ከመከላከል አንጻር ክልሎችም በባለቤትነት እንዲሠሩ ለማድረግ በክልል የሚገኙት የወጪ ንግድ ምርት ግብረኃይሎች ተንቀሳቅሰው በመስራት ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

የስጋ አቅራቢዎች ማህበራትን የማጠናከር ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ ከመንግሥት በኩልም አንዳንድ ፖሊሲዎችን የማሻሻል ተግባር እየተካሄደ እንደሚገኝ አክለዋል፡፡

እስካሁን በሀገሪቱ የሚመረቱ እንስሳትና የስንስሳት ተዋጽኦዎች በስፋት እየተላኩ የሚገኙት ወደ አረቡ ዓለም ሀገራት መሆንኑ በማንሳት፤ የገበያ መዳረሻዎችን በማስፋት በኩል ከካንቦዲያ፣ ቻይና፣ ሲሸልስ አዘርባጃን እና ከሌሎች ሀገራት ጋር በጋራ ለመሥራት ውይይት እየተደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

የኮንትሮባንድ ንግድን፤ ከውጭ ገበያ ይልቅ የሀገር ውስጥ የከብቶች ዋጋ ከፍተኛ መሆን ለዘርፉ የወጪ ንግድ ተግዳሮት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

# በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ተጠያቂነትን ለማስፈን ከ630 በላይ መዝገቦች ተከፍተዋል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ተጠያቂነትን ለማስፈን ከ20 በላይ ትልልቅ ተጠርጣሪዎች ላይ ክስ እንደተመሰረተባቸውና ከ630 በላይ መዝገቦች በፍርድ ቤት ክርክር ላይ እንደሚገኙ ብሄራዊ የፍልሰት ትብብር ጥምረት ጽህፈት ቤት ገለጸ።

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ አብርሃም አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 ዓ.ም በጉዳዩ የተጠረጠሩ ከ20 በላይ ትልልቅ ተጠርጣሪዎች ክስ ተመስርቶባቸው በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ይገኛሉ። ከ630 መዝገቦች በላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት እየታየ ይገኛል።

ከደቡብ ኢትዮጵያ አንስቶ እስከ ደቡብ አፍሪካ በተዘረጋ የሰው ንግድ ሰንሰለት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የነበራቸው ከ20 በላይ ትልልቅ ተጠርጣሪዎች ክስ ተመስርቶባቸው ክርክር ላይ እንደሚገኙም ጠቁመዋል።

የሕግ ማስከበር ሥራው እየተሻሻለ ቢገኝም ተግባሩ ሊጠናከር ይገባዋል ያሉት ኃላፊው፤ አሁንም ዋናዎቹን ደላሎች ከመያዝ፣ ግንኙነታቸውን ከመበጣጠስ፣ በመልማዩችና በመዳረሻ ሀገራት ባሉ ተቀባዩች ያለውን ትስስር በማፍረስ በኩል ብዙ የሚቀሩ ሥራዎች እንዳሉ አመልክተዋል።



አቶ አብርሃም አያሌው

ሀገር ውስጥ በሁሉም አካላት ጠንካራ ትብብር ማድረግ፣ ዓለም አቀፍ ትብብርን ማጠናከር እና ተጎጂዎች በፖሊስ ጣቢያ መጥተው ከሚተገበረው የወንጀል ምርመራ አሠራር መውጣት መፍትሄ መሆኑንም ነው የተናገሩት። ይህንን ለመተግበር ጠንካራ እና ቅንጅታዊ አሠራር መዘርጋት እንደሚገባ ተጠቁሟል።

ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሉን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ከወንጀል ተሳታፊዎቹ የበለጠ የተደራጀ አቅም እና ቅንጅት መፍጠር ያስፈልጋልም ብለዋል።

ድርጊቱን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ክልሎች አባል የሆኑበት ብሄራዊ ምክር ቤት መቋቋሙን፤ በፌዴራል ደረጃ በፍትህ ሚኒስቴር የሚመራ ብሄራዊ የትብብር ጥምረት የፍልሰት አስተዳደር መዘርጋቱንም ኃላፊው ጠቁመዋል።

እንደ አቶ አብርሃም ገለፃ፤ አሁንም ዜጎች በበረሃ ለማቋረጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ለስቃይ እና ለሞት ይዳረጋሉ። ከግንዛቤ ፈጠራው ጎን ለጎን፤ ደላሎችን፣ መልማዮችን፣ አዘዋዋሪዎችን ለሕግ በማቅረብ መደበኛውን ፍልሰት የሚያበረታቱ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል። ወንጀሉን በደህንነት መረጃ ጥናት ላይ በመመስረት የወንጀለኞቹን መረብ ሊበጣጥስ የሚችል ሥራ መሠራት አለበት።

የዜጎች በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር እንቅስቃሴ የሀገር ገጽታ የሚያበላሽ፣ አንገት የሚያስደፋ ከፍተኛ ችግር ያለበት በመሆኑ ብዙ ሥራ መሠራት አለበትም ሲሉ አክለዋል።

500 ሺህ ሰዎችን በሕጋዊ መንገድ ለሥራ ወደ ውጭ ሀገር ለመላክ በመንግሥት የተቀመጠው እቅድ በሕገ ወጥ መንገድ የሚደረገውን እንቅስቃሴ በከፍተኛ መጠን በመቀነስ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣልም ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የእሁድ ገበያን በማጠናከርና አዳዲስ ስልቶች በመተግበር የዋጋ ንረት የሚፈጥረውን ችግር ማቃለል ይገባል!

የሸቀጦች ዋጋ ንረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻቀበ ይገኛል። ዓለም አቀፋዊ የምጣኔ ሀብት ምክንያቶች እንዲሁም የሩሲያና የዩክሬን ጦርነት በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነት እንዲባባስ ካደረጉ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸው ሲገለፅ ቆይቷል። ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ግን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች በዋጋ ግሽበቱ ክፉኛ ተጎጂ ሆነዋል።

መንግሥት ይህንን ችግር ለመፍታት በርካታ የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጦ መተግበር ከጀመረ ሰነባብቷል። መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦች ከውጪ ሲገቡም ሆነ ሀገር ውስጥ ሲገበዩ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲሆኑ በመወሰን መንግሥት የሚያገኘውን ትልቅ ገቢ ትቶ የዋጋ ጫናውን ከሸማቹ ኅብረተሰብ ላይ ለማቃለል ጥረት ተደርጓል፡፡

ይሁን እንጂ ኃላፊነት የማይሰማቸው ነጋዴዎች ምርት ያለአግባብ በማከማችትና እጥረት ያለ በማስመሰል የሚፈጥሩት ኢኮኖሚያዊ ምክንያት የለሽ የዋጋ ንረት እንዲሁም በደላላዎችና ሕገ-ወጥ የንግድ ተዋንያን አማካኝነት ያለው የተንዛዛ የግብይት ሂደት በምግብ ሸቀጦች ላይ እየተከሰተ ያለውን የዋጋ ንረት ለማርገብና ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያሳድረውን ጫና በሚፈለገው መልኩ ለማቃለል አልተቻለም።

ከዚህ አንጻር የቅዳሜና እሁድ ገበያ በተለይም ያለ ኢኮኖሚያዊ ምክንያት እየጨመረ ያላውን የዋጋ ንረት በማርገብ ረገድ ትልቁን ሚና ተጫውቷል። አምራቾች ሰፊ የገበያ ዕድል፣ ሸማቾች ደግሞ ያለደላላ ጣልቃ ገብነት ባጠረ የግብይት ሂደት በተመጣጠነ ዋጋ እንዲሸምቱ አስችሏል።

የቅዳሜና እሁድ ገበያ በቅርበት ባለባቸው አካባቢዎች የግብርና እና የፋብሪካ ምርቶች በአጭር የግብይት ሂደት ከአምራቹ በቀጥታ ለሸማቹ በተመጣጠነ ዋጋ የሚቀርብበት ሁኔታ በዋጋ ንረቱ ቀጥተኛ ተጎጂ ለሆነው የማኅበረሰብ ክፍል የተወሰነ እፎይታን ፈጥሯል። በመሆኑም ግብይቱ ከመደበኛው ገበያ ዋጋ ቅናሽ በበለጠ ተስፋፍቶ መቀጠል አለበት። ጥረቱና ጅምሩ መልካም ሆኖ ሳለ ግን የግብይት ቦታዎቹ ውስን ከመሆናቸው የተነሳ ኅብረተሰቡ ርቀት ያለው መንገድ የታክሲ ትራንስፖርት ከፍሎ በመሄድ የሚያገኘው ገበያ እምብዛም ተጠቃሚ አያደርገውም። ስለሆነም መልካምን ጅምር በማስፋት ሁሉንም የማኅበረሰብ ክፍል ተጠቃሚ ለማድረግ ግን አሁን ካለው በተጨማሪነት በየአካባቢው የግብይት ማዕከላት በመክፈት መስፋፋትና መጠናከር ይኖርባቸዋል፡፡

ምክንያቱም ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ የመጣው የዋጋ ንረት በማኅበረሰቡ ላይ የሚፈጥረውን ጫና ለመቀነስ መንግሥት ከቀየሰው የመፍትሔ አማራጭ በተጨማሪ የግብርና እና የፋብሪካ ምርቶች ይበልጥ ተደራሽ የሚሆኑበትን አዳዲስ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ ይገባል። በዚህ ረገድ ለገበያ የሚያቀርቡትን የምርትና አገልግሎት አይነት ለማስፋትና የግብርና ምርቶችን ከገበሬው ማሳ ላይ ገዝቶ ለማቅረብ የሚታይን የፋይናንስ ችግር ለማቃለልም የበለጠ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል።

መንግሥት የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራትን የፋይናንስ ችግር ለማቃለል እየሠራ ቢሆንም ካለው ከፍተኛ ፍላጎት አንፃር ባለው አቅም ሁሉ ብዙ መጨመርን ይጠበቃል። የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሕዝብ አገልጋይ እንደመሆናቸው መጠን አበዳሪ የፋይናንስ ተቋማት ብድር የሚሰጡበትን ቢሮክራሲ በማቃለልና ብድር በመስጠት ተቀራርበው በመሥራት ሊደግፉ ይገባል፡፡

የቅዳሜና እሁድ ገበያ የዋጋ ንረትን በማርገብ ረገድ ያለው ፋይዳ የጎላ መሆኑ ወደሌሎች ክልሎች ተደራሽነቱን የማስፋት ሥራ ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን አዲስ ስልት ነድፎ መንቀሳቀስ የግድ ይላል። ከዚህ ጎን ለጎን አቅርቦቱን ለማሳደግ እና ለሌሎች ወጣቶችም የሥራ እድል ለመፍጠርም ማሳ ላይ ሰፊ ሥራ ሊሠራ ይገባል።

የከተማ አስተዳደር፣ የክልልና በየተዋረዱ ያሉ የዘርፉ አስፈፃሚ አካላትም የቅዳሜና እሁድ ገበያ ተደራሽነትን ለማስፋት ብዙ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም መንግሥት የዘረጋው የእሁድ ገበያ ሊበረታታና በሌሎች አማራጮች ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዐምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከሀገራዊ ምክክሩ ሁላችንም እናተርፋለን

ሜላት ኢያሱ

አበው የምክርን ወይም የመመካከርን አስፈላጊነት ሲያስረዱ ‹‹ምከረው… ምከረው ፤ እምቢ ካለ መከራ ይምከረው›› ይላሉ። እኛ ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶች፣ ባሕሎችና ወጎች ያሉን ሕዝቦች ነን። በአባቶቻችን ምክር ተግሳጽና ቁጣ እየታረቅን/ እየተስተካከልን ፍቅራችንን እና አንድነታችንን ጠብቀን የኖርን ሕዝቦች ነን። ቿንጉርጉር ማንታችንን ጸንቶ የሚኖር፣ ፈጣሪያችንን የምንፈራና እንግዳ ተቀባይ ሕዝቦች መሆናችንም በታላላቆቹ የክርስትና እና የእስልምና ቅዱሳት መጽሐፍት ላይ አስቀድሞ የተነገረልን ነን።

ከረዥም ዘመን አብሮነታችን የተነሳ ቋንቋዎቻችን፣ ባሕሎቻችን፣ ወጎቻችንና አኗኗራችን ተወራርሰዋል። ከዚህ አለፍ ሲልም እርስ በእርሳችን በደም ተሳስረናል። በዚህ የተነሳ የአንዱ ብሔረሰብ ባሕልና የአኗኗር ሥርዓት ይነስም ይብዛም በሌላው ብሔረሰብ ውስጥ ይንጸባረቃል። ይህ ማለት እያንዳንዱ ብሔረሰብ ራሱንም ሌላውንም ብሔረሰብ ሆኖ ተሳስቦና ተፋቅሮ ኖሯል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር አንዱ ብሔረሰብ ከሌላው ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆኖ ይኖራል ማለት ነው፡፡

ይህ ሁለንተናዊ የተወራራሽነት ባሕሪ የአንድነ ታችንን ካስማ እያጠናከረ እዚህ ድረስ አዝልቆናል። ወደፊትም አብሮን ይኖራል። ብሔረሰባዊ ማንነታ ችንና ኅብረ ብሔራዊ አንደነታችን ሳይጋጩብን ብዙ ዘመናትን ተሻግረን እዚህ የደረስንባቸው ምስጢሮቻችን ብዙ ናቸው። ከነዚህም ሃይማኖታዊና ባሕላዊ እሴቶቻችን ግንባር ቀደሙን ቦታ ይይዛሉ።

በረዥሙ የአብሮነት ጉዟችን ውስጥ መንገዶቻችን ሁሉ አልጋ በአልጋ ነበሩ ማለት አይቻልም። በሀገረ መንግሥት ምሥረታ ሂደትም ይሁን በሌላ ምክንያት ኢትዮጵያ እንደ የትኞቹም የዓለም ሀገራት ማኅበራዊ ግጭቶች ሳይከሰቱባት እዚህ የደረሰች ሀገር አይደለችም፤ እንኳንስ በተለያዩ ብሔረሰቦች መካከል ይቅርና በአንድ ብሔረሰብ ውስጥም ግጭቶች ተከስተው እንደነበር የታሪክ መዛግብት ይናገራሉ። ለዚህ ደግሞ እንደ ዘመነ መሳፍንት አይነቶቹንና በየአካባቢው በነበሩ ገዢዎች መካከል የተፈጸሙ የእርስ በእርስ ጦርነቶችን መጥቀስ ይቻላል። ያም ሆኖ ኢትዮጵያ እንደሀገር ይገጥሟት የነበሩ ወለምታዎችን ሁሉ በነባሩ ባሕላዊ ሕክምናዋ እየጠገነች ሕዝቦቿ ሰምና ወርቅ ሆነው እንዲዘልቁ አድርጋለች።

ሆኖም ኢትዮጵያ ዛሬ ወለም ብሏታል። እንደከዚህ ቀደሙ ወለምታዋን ጠግኖ በሁለት እግሯ ለማቆም የሚጥር ሀገር ወዳድ ዜጋ፣ ምሑር፣ ሽማግሌና የሃይማኖት አባቶች አሏት። ዛሬም ቢሆን እነዚህ አካላት ስለሀገር ሰላም ስለአብሮነትና ወንድማማችነት ያልመከሩበት ያልዘከሩበት ጊዜ አልበረም። የሚሰማቸው ጠፍቶ እንጂ ዛሬም እየተጣሩ ነው። ጥሪያቸውን ሰምቶ ባሉት ሀገራዊ ጉዳዮች ቁጭ ብሎ ከመነጋገር ይልቅ ወለምታዋን ወደ ውልቃት፤ ውልቃቷን ወደ ስብራት የሚያባብሱ ቡድኖችና ግለሰቦች እየበረከቱ መጥተዋል። ነገር ግን እነዚህ የጥፋት መንገዳቸው የትም አያደርሳቸውም፡፡

ነባሮቹ የመከባበር፣ የመቻቻል፣ የአንድነት እና የሰላም እሴቶቻችን በሐሰት ትርክት ተሸርሽረው በማኅበራዊ መስተጋብራችን ላይ የሚፈጠረውን ወለምታ የማከም ሚናቸው እየቀነሰ የመጣ ይመስለኛል።

ዋናው ጉዳይ ግን የሃይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የአባገዳዎች እና የሌሎችም ቀና ምክር፣ ተግሳጽና አስታራቂነት ጸንቶ ያለው ነባሩ እሴት፤ በፖለቲከኛ፣ በነፃ አውጪና በምሑር ነን ባዮች፣ በአክቲቪስቶችና በዩቲዩበሮች አፍራሽ አስተሳሰብ የተጠለፈው ኢትዮጵያዊ መገለጫችን ዛሬ አደጋ ላይ መውደቁን ያዙልኝ፡፡

ለሐሰተኛ ትርክቶች ጆሯቸውን እየሰጡ ስንበደል ኖረናል፣ መብታችን እና ጥቅማችን አልተከበረልንም፣ ሕልውናችን አደጋ ላይ ወድቋል፤ እንደሕዝብ ልንጠፋ ነው፣… የሚሉ ቡድኖች በሚፈጥሩት አሉባልታ የተጋመድንባቸውንና የተሳሰርንባቸውን ክሮች ለመበጣጠስ ብዙ ተሞክሯል። ይህ ታዲያ ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችንን የሚያናጉና ኢትዮጵያ እንደሀገር የመቀጠሏን ነገር ፈታኝ ያደረጉ ማኅበራዊ ቀውሶች እዚህም እዚያም እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል።

እያንዳንዱ ብሔረሰብ የሚያነሳቸው በርካታ ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ይኖራሉ። አንዳንዶቹን ብንመለከት እንኳ ‹‹ለወሰን እና ለማንነት ጥያቄዬ መልስ ይሰጠኝ››፣ ‹‹በዚያኛው ሥርዓተ-መንግሥት ተበድያለሁ››፣ ‹‹በዚህኛው ሥርዓተ-መንግሥት ተገፍቼያለሁ››፣ ‹‹ይሄኛው እንጂ ያኛው ባንዲራ አይወክለኝም››፣ ‹‹ያኛው እንጂ ይሄኛው ባንዲራ አይወክለኝም››፣ ‹‹ሕገ-መንግሥቱ ይሻሻልልኝ››፣ ‹‹ሕገ-መንግሥቱ እንዳይነካብኝ›› የሚሉና እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ጥያቄዎች ሀገራችንን አዙሪት ውስጥ ከከተቱ ምክንያቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአንድ ጉዳይ ላይ የሚንጸባረቁ የተለያዩ ፍላጎቶችን ማስታረቅ የሚቻለው ደግሞ በመነጋጋርና በሀሳብ ልዕልና እንጂ በጠብ መንጃ አፈሙዝ ሊሆን አይችልም። በጠብመንጃ አፈሙዝ የሚረጋገጥ አሸናፊነት ወቅታዊ እንጂ ዘለቄታዊ መፍትሔም አይሠጥም። እርግጥ ነው ጥያቄዎቹ ሁሉ አግባብነት የላቸውም ማለት ግን አይደለም። ችግሩ እነዚህንና መሰል የሀሳብ ልዩነቶችን መነሻ እያደረጉ ነፍጥ ማንሳቱና ጉልበተኝነት አሸናፊ የማያደርግ መሆኑን አለመረዳቱ ላይ ነው።

ጠብመንጃ እንደስሙ ሁሉ ጠብን ከማባባስ፣ ትውልድን ከመብላትና ሀገርን ከማፈራረስ ባለፈ የሚነሱ ጥያቄዎችን ሲመልስ አልታየም። ከተሞክሮዎች መረዳት እንደሚቻለው ጦርነት ካጸናቸው ጉዳዮች ይልቅ ሰላማዊ ንግግር ያጸናቸው ጉዳዮች ይበልጣሉ። ለዚህ ደግሞ የሌላ ሀገራትን ወይም የሩቅ ዘመን ታሪክን መጥቀስ ሳያስፈልገን ከሁለት ዓመት በፊት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ሲደረግ የነበረውን ጦርነት መጥቀስ እንችላለን። የጦርነቱ መቋጫ ያገኘው ሰላማዊ ድርድርና ንግግር ነው። ሆኖም በርካታ ዜጎቻችንን አሳጥቶናል። ከፍተኛ የሀገር ሀብት ባክኗል፤ መሠረተ ልማት ወድሟል።

ገና ከትናንቱ ችግር ሳንወጣ፣ የተጣባን በጠመንጃ አፈሙዝ የመፍታት አባዜ ዛሬም በዚሁ አዙሪት ውስጥ እንድንዳክር አድርጎናል። የራሱን መከላከያ ሠራዊት የሚወጋ፣ የራሱን ሕዝብ ለችግር የሚዳርግ ነፃ አውጪነኝ ባይ በየመንደሩ መሽጎ በገዛ ወገኑ ላይ መተኮስን እንደ ትግል ስልት ሲመለከተው ስናይ ወደየት እየሄድን ነው? ያስብላል። የዛሬው ስሜታዊነትና ተራ ጀብደኝነት ልክ እንደትናንቱ ጥሎብን ከሚያልፈው መከራና የኢኮኖሚ ድቀት በዘለለ ጠብ የሚል ፋይዳ እንደማያመጣ ለሁላችንም ግልጽ ነው።

በመሆኑም አሉን የምንላቸውን ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ ማቅረብ በጉዳዩ ላይ መከራከርና በሀሳብ ልዕልና ማሸነፍ ወይም መሸነፍ ዓለም የሚከተለው የሠለጠነ መንገድ ነው። ከዚህ አንጻር መንግሥት በያዝነው ዓመት ሀገራዊ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል። ይህ አጋጣሚ ማዶና ማዶ ሆነው የየራሳቸውን ሀሳብ የሚሠነዝሩ ኢትዮጵያውያን ተቀራርበው እንዲነጋገሩና ለጋራ ሀገራቸው የጋራ መፍትሔ እንዲያፈላልጉ ያግዛል። ልዩነቶቻችንን ማስወገድ የምንችለውና ለሀገራችን እና ለሕዝባችን የሚበጅ ቁምነገር መሥራት የምንችለው በሀሳብ የበላይነት እንደመሆኑም፤ ሀገራዊ የምክክር መድረኩ ‹‹ፈረሱም… ሜዳውም…›› እንዲሉ ለሁሉም በሩን ክፍት ያደረገ ነውና ሀሳብ ያለን ወደ ሜዳው ብንመጣ ብዙ የምናተርፍበት ይሆናል፡፡

# በመዲናዋ ብቻ ይሰጡ የነበሩ የፈጠራ ሥራ ሥልጠናዎች በመላ ሀገሪቱ ተግባራዊ ሊደረጉ ነው

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ብቻ ሲሰጡ የነበሩ የፈጠራ ሥራ ሥልጠናዎችን በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ አስታወቀ። በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የሳይንስ ፌስቲቫል በመጪው ሚያዝያ ወር እንደሚካሄድ ተመላክቷል።

አካዳሚው በ2015 ዓ.ም ክረምት ወቅት ለሁለት ወራት በኤሌክትሮኒክስና በኮምፒዩተር ሳይንስ ሥልጠና ለሰጣቸው 46 የፈጠራ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች የእውቅና መርሃ ግብር አካሂዷል።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ምክትል ሥራ አስፈጻሚ ጥበበሥላሴ ስዩም (ዶ/ር) በመርሐግብሩ እንደገለጹት፤ ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ውጤታማ ተማሪዎችን በማሰባሰብ የፈጠራ ሥራቸውን ለማበረታታት ከ2012 ጀምሮ በክረምት ወቅት በኤሌክትሮኒክስ እና በኮምፒውተር ሳይንስ ዘርፍ እያሠለጠነ ይገኛል።

በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ እየተሰጠ የሚገኘውን ሥልጠና እና የሥራ ፈጠራ ከቀጣይ ዓመት ጀምሮ በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ ይደረጋል ያሉት ዶክተር ጥበበ ሥላሴ፤ በሀገሪቱ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ሳይንስን ባህል እንዲያደርጉ እና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሳይንሳዊ መንገድ መፍታት እንዲችሉ ያግዛል ብለዋል።

በቀጣይ ጊዜያትም ሥልጠናው በግብርና፣ በጤና፣ በማህበራዊ ሳይንስና በሌሎች ዘርፎች መሰጠት እንደሚጀምር አስታውቀዋል።

እንደ ዶክተር ጥበበ ሥላሴ ገለጻ፣ አዳሚው በሳይንስ ትምህርቶች ዙሪያ የተማሪዎችን ዝንባሌ መገንባትና የመፍጠር አቅማቸውን ለማሳደግ በርካታ ሥራዎችን እየሠራ ነው። በዚህም በ2015 ዓ.ም ክረምት ወቅት ለሁለት ወራት በኤሌክትሮኒክስና በኮምፒዩተር ሳይንስ ሥልጠና ለሰጣቸው 46 የፈጠራ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች እውቅና መስጠቱን አስረድተዋል።

ዕውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎቹ ከአዲስ አበባ ከተማ 10 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡና በ16 የተለያዩ ዘርፎች የሠለጠኑ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በየዓመቱ በክረምት ወቅት የፈጠራ ክህሎትና ዝንባሌ ያላቸውን ተማሪዎችን በመመልመል በንድፈ ሃሳብና በተግባር የተደገፈ የአጭር ጊዜ ሥልጠና እየሰጠ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

እውቅና የተሰጣቸው ተማሪዎች በቀጣይም የፈጠራ ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ ለማስቻል አካዳሚው የተለያዩ ድጋፎች እንደሚያደርግላቸው እና ሥልጠናውን በመላ ሀገሪቱ ተደራሽ በማድረግ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስገንዝበዋል።

በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ተጠባባቂ ዳይሬክተር አቶ መስፍን እንግዳ ወርቅ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ማዕከሉ ከ10ኛ እስከ 12ኛ የክፍል ደረጃ ላሉ ተማሪዎች የፈጠራ ሥራቸውን ለማበረታታት የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል።

በዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ውድድሮች አበረታች ውጤት ከማስመዝገባቸውም ባለፈ የሠሩትን የሙከራ ፈጠራ ሥራ ዕውን ለማድረግ ከዓለምና ሀገር አቀፍ ድርጅቶች ጋር በጋራ እየሠሩ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የሳይንስ ፌስቲቫል በመጪው ሚያዝያ ወር እንደሚካሄድ የጠቆሙት አቶ መስፍን፤ ሳይንስን ሁሉም ማህበረሰብ እንዲገነዘበው ይረዳል ብለዋል።

በፌስቲቫሉ ሳይንስ ላይ ትኩረት ያደረገ የፓናል ውይይት፣ ሳይንስን የሚያስረዱ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ የሳይንስ ትያትርና ፊልሞች የሚቀርብ ሲሆን፤ በዘርፉ የሚሠሩ ተቋማት እና ግለሰቦች ይሳተፉበታል ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

## በበጀት ዓመቱ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በግብርና ሚኒስቴር የሆርቲካልቸር ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አብደላ ነጋሽ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተያዘው በጀት ዓመት 379 ነጥብ 49 ቶን የአበባ፣ የፍራፍሬ፣ የአትክልትና እጸጣዕም፣ የእንስትና ስራስር ምርቶችን ወደተለያዩ የውጭ ሀገራት ለመላክ ታቅዶ እየተሠራ ይገኛል።

በበጀት ዓመቱ ወደውጭ ከሚላኩት የሆልቲካልቸር ምርቶች 720 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ለማግኘት ታቅዶ፤ በሩብ ዓመቱ ከ129 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ማገኘት መቻሉን አስታውቀዋል።

ገቢው የተገኘው ከአበባ፣ ከአትክልትና ፍራፍሬ፣ ከእንሰት፣ ከስራስር እና መዓዛማ ከሆኑ እጸዋቶች መሆኑን ገልጸው፤ ከአበባ ምርት 112 ነጥብ 12 ሚሊዮን ዶላር፣ ከፍራፍሬ ከአራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ መገኘቱን ተናግረዋል።

ከአትክልትና እጸጣዕም ምርቶች ከዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር በላይ፣ ከእንሰት እና ስራስር ምርቶች ከአራት ሚሊዮን በላይ ዶላር ገቢ የተገኘ ሲሆን፤ በአጠቃላይ በሩብ ዓመቱ 72 ሺህ 788 ነጥብ 82 ቶን የሆልቲካልቸር ምርት ወደተለያዩ የውጭ ሀገራት ተልኮ 129 ነጥብ 56 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ማግኘት እንደተቻለ ገልጸዋል።

ከምስራቅ አፍሪካ ጅቡቲና ሶማሊ፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ፣ ሩሲያ፣ ኔዘርላንድ እና ሌሎች ሀገራት ዋና ዋናዎቹ የሆልቲካልቸር ምርት መዳረሻ ሀገራት መሆናቸውን አመላክተዋል።

የሆልቲካልቸር ዘርፉ ለሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬን ለማስገኘት፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና የገበያ ትስስርን ለማሳደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው ቢሆንም መንግሥትና ባለድርሻ አካላት



አቶ አብደላ ነጋሽ

እንደሌሎች ዘርፎች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩበት አይደለም ብለዋል።

ከዚህ በፊት ያሉት የግብርና ፖሊሲዎች የሆልቲካልቸር ዘርፉን ውጤታማ የሚያደርጉ አይደሉም ያሉት አቶ አብደላ፤ የፖሊሲና የስትራቴጂ ማሻሻያ ሊደርግለት ይገባል ብለዋል።

ከዚህ በፊት የተጀመሩ የፖሊሲ ማሻሻያ ሥራዎች ከግንዛቤ ማነስ የተነሳ ችላ መባላቸውን አስታውሰው፤ የተጀመሩትን የፖሊሲ ማሻሻያዎች አጠናክሮ በማስቀጠል ዘርፉን በማሳደግ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ እንደሚገባ አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ የሚፈጠሩ የጸጥታ ችግሮች፣ የመሬት እጥረት፣ ለዘርፉ ትኩረት አለመሰጠቱ፣ ምርት ከተሰበሰበ በኋላ የሚቀዘቅዝበት ቦታና የማጓጓዣ እጥረት ለዘርፉ ውጤታማ አለመሆን ተግዳሮት መሆናቸውን አስረድተዋል።

## ከ610 ሺህ ኩንታል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አምስት ቢሊዮን ብር በጥሬ ገንዘብም እንዲደርሳቸው መደረጉንም አመልክተዋል።

ድጋፍ የተደረገው በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በግጭት እንዲሁም የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል ተብለው ለተለዩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚገኙ ነው።

ርዳታው ለሁለተኛ ዙር የተደረገ ሲሆን ባለፉት 15 ቀናት ነው የተከናወነው። በመጀመሪያ ዙር አራት ሚሊዮን ለሚጠጉ ሰዎች የሰብዓዊ ድጋፍ ተደርጓል።

ከዚህ በፊት የዓለም ርዳታ ድርጅት እና መሰል አጋር አካላት ርዳታ መገኘታቸውን ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ለደረሰባቸው ሰዎች ከመጠባበቂያ እህል ክምችት ለዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል።

ኮሚሽኑ የቅድመ ማስጠንቀቅ ሥራ ይሰራል ያሉት አቶ አታለለ፤ ሰው ሰራሽ እና የተፈጥሮ አደጋ ለደረሰባቸው ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ የማቅረብ ሃላፊነት እንዳለበት አንስተዋል።

አሁንም ርዳታ እየተደረገ ይገኛል። በተቻለ አቅም ከመጠባበቂያ ምግብ ክምችት እየገዛ ካስቀመጣቸው ምግብ ክምችቶች የሰብዓዊ ድጋፍ እያደረሰ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ምላሽ ለመስጠት በየጊዜው የመጠባበቂያ ክምችት አቅምን በማሳደግ ላይ ትኩረት መደረጉን ያመላከቱት አቶ አታለለ፤ የሰብዓዊ ድጋፍ ተልኮ በጸጥታ ችግር ምክንያት ድጋፉ ሳይደርስ መዘግየት መኖሩን እንደተግዳሮት አንስተዋል።

በርቀት እና በጸጥታ ችግር ምክንያት ለመድረስ አስቸጋሪ በነበሩ ትግራይ ክልል፣ ዋግህምራ እና ሰሜን ጎንደር አካባቢዎች መንግሥት በሙሉ አቅሙ በመጠቀም የሰብዓዊ ድጋፍ እያደረሰ መሆኑን አስረድተዋል።

ሰብዓዊነት የሚሰማው የትኛውም ግለሰብ በአካባቢው ያሉ ተፈናቃዮችን እና ርዳታ ፈላጊዎችን ማበረታታት ይገባዋል ብለዋል።

መንግሥት በጸጥታ መዋቅሩ በመታገዝ ጭምር የሰብዓዊ ድጋፍ የማቅረብ ኃላፊነትን እየተወጣ ነው። ሰብዓዊነት የሚሰማው፣ ኃላፊነት ያለው እና ወገኑን የሚወድ ሁሉ ለወገኑ አለኝታነቱን ማሳየት እና የመደጋገፍ ባህሉን ማጠናከር እንደሚጠበቅበትም መክረዋል።

## ቴክኒክና ሙያ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የ2016 ዓ.ም የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኞችን እንደሚቀበሉ የገለጹት ዶክተር ተሻለ፤ በዘንድሮው ዓመት 600 ሺህ ተማሪዎችን ተቀብሎ ለማሠልጠን የሚያስችል በቂ የትምህርት ግብዓት ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል።

በቴክኒክና ሙያ ሥርዓተ ትምህርት በየዓመቱ ከሚሠለጥኑት የመደበኛ ፕሮግራም ሠልጣኞች በተጨማሪ በአጫጭር ሥልጠናዎች ሁለት ሚሊዮን ዜጎች የሚሠለጥኑበት ዘርፍ መሆኑን አስታውቀዋል።

የቴክኒክና ሙያ ሥርዓት ሰፊና በርካቶችን የሚያገለግል መሆኑን ገልጸው፤ ዘርፉን ዲጂታላይዝ ለማድረግ የሚያስችል የቴክኖሎጂ ግብዓት እየተሟላ መሆኑንም አስረድተዋል።

የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሩክ ከድር በበኩላቸው፤ ኢንስቲትዩቱ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሠልጣኞችንና አመራሮችን የሚያሠለጥን በመሆኑ ከመላ ሀገሪቱ ለሥልጠና የሚመጡ ሰዎች በመመልመል ለማሠልጠን የሚያስችል ዝግጅት እያከናወነ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

በኢንስቲትዩቱ አዲስ የቅበላ ፖሊሲ የተዘጋጀ መሆኑን በመግለጽ፤ በርካታ ሠልጣኞችን ተቀብሎ ለማሠልጠን የሚያስችል አቅም መፈጠሩን አመልክተዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከደረጃ 6 ጀምሮ የሚገኙ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠናዎችን እንዲሁም በተለያዩ የሥልጠና ደረጃዎች ተማሪዎችን ተቀብሎ ያሠለጥናል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ሠልጣኞችን ብቃት ያላቸው ሙያ እንዲሆኑ የሚያስችል ትምህርት ይሰጣል ብለዋል።

በአጫጭር ሥልጠናዎች በርካታ ዜጎችን በተለያዩ ሙያዎች በማሠልጠን ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በአዲስ አበባና በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት ሠልጣኞችን በመቀበል እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በሀገሪቱ በርካታ የመንግሥትና የግል የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት መኖራቸው የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ማዕከላትን የሥልጠና ጥራትና ፍትሐዊ ተደራሽነትን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ሲሉ ገልጸዋል።

## “ኢትዮጵያ በበጋ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እየተሠራባቸው እንደሆነና የግብዓት ግዥዎች እንደተፈጸሙ ያነሱት ሚኒስትሩ፤ በአሁኑ ሰዓት የዝግጅት ምዕራፎች ተጠቃለው ወደትግበራ እየተገባ ሲሆን የመጀመሪያውን የአፈር ማዳበሪያ የጫኑ መርከብ ጅቡቲ ወደብ መድረሷን ተናግረዋል።

የተጀመሩ ተግባራትን በላቀ ደረጃ በማስቀጠልና ተሞክሮዎቹን በመቀመር በአርሶ አደሮች ዘንድ እንዲተገበሩ ለማድረግ የተጠናከረ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት እንዲሁም ሌሎች የግብርና ልማት ሥራዎችን በተቀላጠፈ መልኩ ለማከናወን የሚረዱ ድጋፎችን ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ወረዳዎች በግብርና ዕድገት ፕሮግራም የተገኘውን ውጤትና የተጀመሩትን የልማት ሥራዎች በተጠናከረ መልኩ እንዲያስቀጥሉ ተሸከርካሪዎች አስፈላጊ ናቸው ብለዋል።

ተሸከርካሪዎቹ ለክልሎችና ለወረዳዎች የፕሮግራም ማኔጅመንት ዩኒት ክትትልና ድጋፍ አገልግሎት በመስጠት የአፈፃፀም አቅምን ያጎለብታሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ በፕሮግራሙ የተጀመሩ ሥራዎች ሳይስተጓጎሉ እንዲቀጥሉ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖራቸው አመልክተዋል።

በግብርና ዕድገት ፕሮግራም በ10 ክልሎችን በአንድ ከተማ አስተዳደር ስር ለሚገኙ ለ53 ወረዳዎችና ለገጠር ሥራ ምቹ የሆኑ 97 መኪናዎችና 350 የሞተር ብስክሌቶች ሲሆኑ አምሥት ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር ወጪ ተደርጎባቸዋል ነው ያሉት።

የአየር ንብረት አፈጻጸም መሬት አያያዝ ፕሮግራም በ11 ክልሎች ውስጥ በሚገኙ 501 ወረዳዎች በ500 ሚሊዮን ዶላር እየተተገበረ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሥራው ከዓለም ባንክ በተገኘ ድጋፍ እየተከናወነ የሚገኝ ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ግርማ ገለፃ፤ በአጠቃላይ በሁለቱም ፕሮጀክቶች ድጋፍ የተደረጉ ቁሶች አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ገደማ ወጪ ተደርጎባቸዋል።

የተደረገው ድጋፍ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የአደራ መልዕክት አስተላልፈው ድጋፉ ከዓለም ባንክና ሌሎች አጋር አካላት እንደተገኘ ሚኒስትሩ አውስተዋል።

በሥነሥርዓቱ ላይ የተገኙት በዓለም ባንክ የኢትዮጵያ፣ የሱዳን፣ የደቡብ ሱዳንና ኤርትራ ዋና ዳይሬክተር ኡስማኔ ዲዮኔ በበኩላቸው፤ የዓለም ባንክ በግብርናው ዘርፍ ለኢትዮጵያ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልፀው ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ከሰብ ሰሀራ በታች ካሉ ሀገራት አመርቂ ውጤት እያስመዘገበች እንደሆነ ጠቁመዋል።

የሁለተኛው የግብርና ዕድገት ፕሮግራም ዓላማ በተመረጡ ወረዳዎች አነስተኛ አርሶ አደሮች፣ ወጣቶችና ሴቶችን ባሳተፈ መልኩ ምርታማነት ማሳደግና ምቹ የገበያ ሁኔታ በመፍጠር የተሻለ ንጥረ ምግብ ይዘት ያላቸው የተለያዩ የሰብልና የእንስሳት ዓይነቶች በአርሶ አደሮች ማሣ እንዲመረቱ በማድረግ በቤተሰብ ደረጃ ያለውን የአመጋገብ ሥርዓት ማሻሻል መሆኑም ተገልጿል።

ድጋፉን የየክልል ግብርና ቢሮ ኃላፊዎች የተረከቡ ሲሆን ተሸከርካሪዎቹን ለተሰጡበት ዓላማ ብቻ እንዲያውሉ መልዕክት ተላልፏል።

# አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ያለው የበጋ መስኖ

**ፍሬሕይወት አወቀ**



በኢትዮጵያ የግብርና ምርትን ለማሳደግና የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ ከተነደፉት ስትራቴጂዎች መካከል የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ተጠቃሽ ነው። የመስኖ ልማት ሥራን በማስፋፋት ረገድም በሀገሪቱ የምግብ ዋስትና ክፍተት ባለባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች በመስኖ ልማት በመድረስ በምግብ እራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግን ዓላማ አድርጎ የሚሠራ ነው።

የመስኖ ልማት ሥራ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥን በመዋጋት የምግብ ዋስትናን በማሻሻልና የአርሶ አደሩን ገቢ መጨመር የሚያስችሉ ሥራዎችን በመተግበር የመስኖ ተጠቃሚ አርሶ አደሮችን የኑሮ ደረጃ በዘላቂነት መለወጥን ዓላማ አድርጓል። ከዚህ አንጻር በተለይም የበጋ መስኖ ልማት ሥራ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በአሁን ወቅት በተለያዩ አካባቢዎች ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት በመስኖ ሥራ ያደረገችው ፈርጀ ብዙ ጥረት ከድህነት ለመላቀቅ የሚያስችላትን ትክክለኛ አቅጣጫ መያዝ እንደቻለች ያመላከተ ነው። አገሪቷ ያላትን የመሬትና የሰው ኃብት በመጠቀም ግብርና መር የኢኮኖሚ ፖሊሲና ስትራቴጂ ነድፋ በመሥራት በተለይ ባለፉት አሥር ዓመታት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ እንደቻለች መረጃዎች ያመላክታሉ። በአገሪቱ በመጀመሪያው የአምስት ዓመት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ የተመዘገበውን ውጤት መነሻ በማድረግ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራም ተጠናክሮ የቀጠለ መሆኑ ይታወቃል።

በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ወዲህ መንግሥት ለበጋ መስኖ ስንዴ በሰጠው ከፍተኛ ትኩረት የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል። መንግሥት ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በሰጠው ትልቅ ትኩረትም ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት በሃገር ውስጥ ለመተካት ሰፊ ርብርብ አድርጓል። በዚህም አበረታች ውጤት መመዝገብ ችሏል። እንደ ሀገር ተጠናክሮ የቀጠለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ አሁን በተለይም የውሃ አማራጭ ባለባቸው አካባቢዎች መስኖ እየሰፋና እየተለመደ መጥቷል። በዚህም በመስኖ እየለማ ያለው የመሬት ስፋት ከዓመት ዓመት እያደገ መምጣቱን የግብርና ሚኒስቴር መረጃ ያመላክታል።

በሀገሪቱ በአሁን ወቅት ተጠናክሮ የቀጠለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ አበረታች ውጤት እየታየበት እንደሆነ የጠቀሱት የግብርና ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ከበደ ላቀው እንደሚሉት፤ ከበጋ መስኖ ልማት ሥራ ጎን ለጎን መደበኛ የሆነው የመስኖ ሥራም በአግባቡ እየተከናወነ ይገኛል። በተለይም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ በሁሉም ክልሎች በሚባል ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በስፋት እየተሠራ ነው። በመሆኑም በዘንድሮ በጀት ዓመት እንደ ሀገር ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ለማረስ ታቅዷል። ከሚታረሰው ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥም 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል ነው ያሉት።

እሳቸው እንዳሉት እንደ አገር በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የታቀደውን ዕቅድ ለማሳካትም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው። በተለይም ከታች ከአርሶ አደሩ ጀምሮ በየደረጃው ለሚገኙ አመራሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በመሥራት የመስኖ ልማት ሥራ ካለፈው ዓመት በበለጠና በተሻለ ሁኔታ ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሆነና ለዚህም የተለያዩ ጥረቶች መደረጋቸውን ተናግረዋል።

የክረምቱ ወቅት እያለፈ የበጋው ወቅት እየመጣ ባለበት በዚህ ወቅት በተለይም የበጋ መስኖ ስንዴን ለማልማት ሰፊ ጥረት እየተደረገ ነው ያሉት አቶ ከበደ፤ ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ መደበኛ የሆነው የመስኖ ልማት ሥራም እየተከናወነ እንደሆነ ነው ያስረዱት። እሳቸው እንዳሉት፤ በመደበኛው የመስኖ ልማት ሥራ በአሁን ወቅት ሽንኩርት፣ ቲማቲም፣ ድንች፣ ጎመን፣ አቦካዶና የመሳሰሉ ምርቶች እየለሙ እንደሆነ ገልጸው፤ በሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የሚለማው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራም ከመደበኛው የበጋ መስኖ ሥራ ውጭ እንደሆነ ነው ያብራሩት።

በአሁን ወቅትም ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ አስፈላጊው የሆኑ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ተጠናቀው የተሠሩ በመሆናቸው ወደ ተጨባጭ ተግባራት መሸጋገር ተችሏል። ያሉት አቶ ከበደ፤ እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2016 ባለው ጊዜ ውስጥ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያና በአፋር ክልል ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የቅድመ እርሻ ሥራ ተሠርቷል። በክልሎቹ የተሠራው የቅድመ እርሻ ሥራን አስመልክቶም የእርሻ ሥራው በዘመናዊና በባሕላዊ መንገድ መከናወኑን ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት 738 ሺ 430 ሄክታር መሬት በባሕላዊ መንገድ የታረሰ ሲሆን፤ በዘመናዊ መንገድ ወይም በትራክተር ደግሞ 193 ሺ 269 ሺ ሄክታር መሬት ታርሷል። ከዚሁ የቅድመ እርሻ ሥራ ውስጥ እስካሁን ባለው 334 ሺ 937 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈን እንደቻለም አመላክተዋል፡፡

የቅድመ እርሻ ሥራው በሌሎች ክልሎችም ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሆነና አጠቃላይ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት መታቀዱን የጠቆሙት አቶ ከበደ፤ አጠቃላይ የበጋ መስኖ ሥራው ሁሉንም ክልሎች ያማከለ እንደሆነ ነው የገለጹት። ከላይ ከተጠቀሱትና ወደ እርሻ ሥራ ከገቡት ክልሎች ውጭ የሚገኙ ቀሪ ክልሎችም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን ለማከናወን የቅድመ እርሻ ሥራዎች እንቅስቃሴ መጀመር እንደቻሉ ተናግረዋል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ካለፈው ዓመት በተሻለ ለመሥራት ከፍተኛ ጥረት መደረጉን የጠቀሱት አቶ ከበደ፤ ከእነዚህም መካከል የአርሶ አደሩን ግንዛቤ ማሳደግ ትልቁ ሥራ እንደነበር አስታውሰዋል። ከዚህ በተጨማሪም ወደ በጋ መስኖ ሥራ ያልገቡ ክልሎችን በማስገባት፣ በሠርቶ ማሳያ፣ በልምድ ልውውጥ፣ በአርሶ አደር ማሳ ላይ በተደረጉ የመስክ ጉብኝቶችና ሌሎች ጥረቶችን በማድረግ አጠቃላይ የአመራሩንና የአርሶ አደሩ ግንዛቤ በማሳደግ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከዓመት ዓመት ውጤት ማስመዝገብ እንዲችል ሆኗል ነው ያሉት፡፡

የውሃ አማራጮች እና ሰፋፊ መሬቶች እያሉ መሬት ጦም አይደር በሚል በተለይም የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ሰፊ የንቅናቄ ሥራዎች መሠራታቸውን የጠቀሱት አቶ ከበደ በተለይም ከላይ እስከታች ያለው አመራር ትልቅ ትኩረት ሰጥቶት መሥራት በመቻሉ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ ነው የገለጹት። የተመዘገበው ውጤትም አርሶ አደሩን የበለጠ እንዲሠራ ያነሳሳው እንደሆነና ከዚህ በተጨማሪም የአፈር ማዳበሪያ፣ ኬሚካልና ምርጥ ዘርን ጨምሮ የተለያዩ ግብዓቶችን ለአርሶ አደሩ በቶሎ ተደራሽ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል። ይህም ተጠናክሮ የሚቀጥል በመሆኑ በቀጣይ ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የሀገር ውስጥ ፍጆታን ለማሟላት አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል ነው ያሉት፡፡

በቀጣይም የውሃ አማራጮች ባሉበት አካባቢዎች አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን በማሟላት ለአርሶ አደሩ እንዴት ተደራሽ ማድረግ ይቻላል የሚለውን በማጥናት የመለየት ሥራ የሚሠራ እንደሆነ የገለጹት አቶ ከበደ፤ ይህም የበጋ መስኖ ሥራው ከዓመት ዓመት ለማስፋትና ለማሳደግ ጠቃሚ እንደሆነ ነው ያመላከቱት። ለዚህም አርብቶ አደሩን ጨምሮ የሚመለከታቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በሙሉ ለበጋ መስኖ ልማት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸውና ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ነው ያስረዱት።

ከበጋ መስኖ ሥራው በተጨማሪም አሁን ባለንበት የመኸር ወቅት በአንዳንድ ቆላማ አካባቢዎች የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ የገለጹት አቶ ከበደ፤ ይህም የደረሱ ሰብሎችን ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብ ለመታደግ ሰፊ ሥራ የሚጠይቅ ነው ብለዋል። በመሆኑም አርሶ አደሩ ከብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ የሚደርሰውን ምክረ ሃሳብ መሠረት በማድረግ የደረሱ ሰብሎችን በቶሎ መሰብሰብ ያለበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ለዚህም የተለያዩ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና ሜካናይዜሽኖችን ማለትም ኮምባይነሮችን፣ በእጅ የሚንቀሳቀሱ አነስተኛ የሆኑ አዳዲስና የተሻሻሉ መሣሪያዎችን በመጠቀም እንዲሁም በቡድን፣ በቤተሰብና በልማት አደረጃጀት በመሆን የደረሱ ሰብሎችን የመሰብሰብ ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ በበኩላቸው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ ከዓመት ዓመት እያደገ መምጣቱንና አበረታች ውጤት እያስመዘገበ ስለመሆኑ ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በተለይም በአገሪቱ የተወሰኑ አካባቢዎች በሚገጥሙ የዝናብ መቆራረጦች ምክንያት የሚፈጠሩ የምርት እጥረቶችን ለማሸፈን ከሚያስችሉ ሥራዎች መካከል የበጋ መስኖ ሥራ አንዱና ዋነኛው እንደሆነ ጠቅሰዋል። ከዝናብ መቆራረጥ ጋር ተያይዞ ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከምርት ውጭ ሊሆኑ የሚችሉ አካባቢዎችን በመስኖ ልማት ሥራ ለመደገፍ ከተለያዩ ክልሎች ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑን ነው ያመላከቱት፡

በአሁን ወቅትም ከመኸር ሥራው ጎን ለጎን የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው ይህም ሁለት አይነት ጠቀሜታዎችን የሚያበረክት እንደሆነ ነው ያመላከቱት። አንደኛው በአሁን ወቅት በሀገሪቱ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ በስፋት እየተለመደና ተጠናክሮ መቀጠል ችሏል። ይህ ሁኔታም በምርትና ምርታማነት ላይ ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ጠቅሰዋል። ሁለተኛው በተለይም ዝናብ በተቆራረጠባቸው አካባቢዎች ላይ በአካባቢው ያለውን የመስኖ አማራጮች በመጠቀም በቶሎ ወደ ምርት ሥራው ለመግባት አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር በመቻሉ አበርክቶው ጉልህ ነው።

እሳቸው እንዳሉት በሀገሪቱ እየሰፋና ተጠናክሮ የቀጠለው የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በሁሉም ክልሎች ተጠናክሮ የሚቀጥል ስለመሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታቸው በዝግጅት ምዕራፍ ባደረገው ግምገማ ማረጋገጥ ችሏል። በመሆኑም በተያዘው በጀት ዓመት ብቻ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ለመሸፈን ከክልሎች ጋር በመግባባት ስምምነት ላይ መድረስ ተችሏል። በመሆኑም በተያዘው በጀት ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ብቻ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሸፈን ይሆናል። ይህም ባለፈው በጀት ዓመት ከተሠራው አንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ ማደግ እንደቻለ አስረድተዋል። ይህም እንደ ሀገር በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተመዘገበ ያለው ውጤት አበረታች እንደሆነና እምርታን ያሳየ ነው ብለዋል፡፡

በዘንድሮው የምርት ዘመን በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከሚሸፈነው ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት 117 ሚሊዮን ኩንታል ምርት የሚጠበቅ እንደሆነ ያመላከቱት ሚኒስትሩ፤ ይህ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በክረምት ወቅት ከምታለማው የስንዴ መጠን ጋር ሲነጻጸር ተቀራራቢ እንደሆነም ተናግረዋል። ባለፈው በጀት ዓመት ሁለት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሄክታር መሬት አካባቢ በመኸር ወቅት የስንዴ ልማትን መሸፈን እንደተቻለ አስታውሰው በዘንድሮ በጀት ዓመት በመኸር ወቅት ብቻ ሦስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በበጋ መስኖ ስንዴ ለመሸፈን ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ እንደሆነ ነው ያመላከቱት።

በበጋ መስኖ እየለማ ያለው የስንዴ ምርት በመደበኛው የእርሻ ሥራ ወቅት ወይም በመኸር ዝናብ ተጠብቆ ከሚሠራው ሥራ ጋር ተቀራራቢ እየሆነ መምጣቱን የጠቀሱት ሚኒስትሩ፤ ይህም ትልቅ እምርታን እያሳየ ያለና በአገሪቱ ያለውን የስንዴ ምርት አስተማማኝ ደረጃ ላይ የሚያደርሰው እንደሆነ ገልጸዋል። አያይዘውም የተጀመረው የበጋ መስኖ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል በመቻሉ በመስኖ የማምረት አቅምን ከዓመት ዓመት እየጨመረ የመጣ መሆኑን እና ዝናብ ባይኖርም በበጋ መስኖ ብዙ መሥራት እንደሚቻል አብራርተዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# በተማሪዎች ውጤት የተንፀባረቀው የመምህራን ምዘና

ግርማ መንግሥቴ

ምዘና ባደጉት ሀገራት ረጅም እድሜ ያለውና የተለመደ አሠራር ነው። ከዚህ አኳያ ምዘና ለሙያ ብቃት፣ ለአሠራር ጥራትና ለአገልግሎት ቀልጣፋነት ያለው ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ የተመረቁ የጤና ባለሙያ አመልካቾች የሙያ ፈቃድ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማቅረብ የሚጠበቅባቸው መሆኑ የምዘና አንዱ ማሳያና በሌሎች ሴክተሮች ውስጥም እንዳለ አመላካች ነው። ወደ ትምህርቱ ሴክተር ሲመጣ ደግሞ ምዘና ለረጅም ጊዜ ስሙ ሲነሳ የነበረ ነው። በሂደት ደግሞ ወደ ሥራ ተገብቶበት ለመምህራን የመመዘኛ ጥያቄዎች ተሰጥተው የምዘና ተግባሩ ተከናውኗል።

በመሠረቱ "ምዘና ለምን?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ከተነሳው ርዕሰ ጉዳይ አኳያና ከተለያዩ ትምህርት ተቋማት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ምዘና ሙያዊ ጥንካሬ እና ድክመቶችን በመለየት የመምህራንን ብቃት ለማሻሻል፤ መምህራን የተማሪዎቻቸውን አቅም ያጎለብቱ ዘንድ ለማስቻል፤ ተጠያቂነትን ለማስፈን፤ በትምህርት ሥርዓቱ የሚፈለገውን የትምህርት ጥራት ለማምጣት፤ በየደረጃው ያሉ መምህራንና የትምህርት ተቋማት አመራሮች ወሳኝ ሚና ያላቸው እንደ መሆኑ መጠን ያንን አቅም ለማዳበር፤ እንዲሁም፣ የትምህርት ሥርዓቱ በተወዳዳሪ መምህራን እንዲሞላ እና የትምህርት ጥራትን ማስጠበቅ የሚያገለግል ሁነኛ የመማር-ማስተማር መሣሪያ ነው።


የመምህርነት ሙያ ቀደም ሲል በሠለጠኑበት እውቀት ብቻ በመጠቀም የሚሠራበት ሳይሆን በየጊዜው የራስን አቅም መገንባትን የሚጠይቅ በመሆኑ ምዘናና የሙያ ፍቃድ የመኖሩ ጉዳይ ያንን አቅም ለመፍጠር ያግዛል። የመምህራን ምዘና በሥራ ያሉትን መምህራን የማብቃት ሥራ መሥራትና አዲስ ወደ ሙያው የሚገቡትንም በሙያ ምዘናው ውስጥ እንዲያልፉ በማድረግ የማስተማር ብቃታቸውን በቀጣይነት ለማረጋገጥ ያስችላል። በአጠቃላይ የመምህራንና ትምህርት ተቋማት ሙያ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ሥርዓት፣ ማለትም ሙያው የሚጠይቀውን ሥነምግባር፣ እውቀት፣ ክህሎትና የተግባራት ክንውን ባካተተ ሁኔታ ተገቢውን ሙያዊ ብቃት ስታንዳርዶችን (professional Competence Standards) የሚያሳይ ሥርዓት መሆኑን ለአዲስ ዘመን ማብራሪያ የሰጡት ባለሙያ ይናገራሉ።

ሌሎች በርካታ የመስኩ ባለሙያዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ እንደሚደመጠው፣ የመምህራንና የትምህርት ተቋማት አመራር ሙያዊ እንቅስቃሴ ዋና ግብ የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻልና ያወቀ ትውልድ መፍጠር ነው። እንደ ትምህርት ሚኒስቴር እምነት ከሆነ ደግሞ ለመምህራንና ለትምህርት የሥራ ኃላፊዎች የሙያ ፍቃድ መስጠትና ማደስ መምህሩንና የትምህርት አመራሩን በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ተግተው እንዲሠሩ ያስችላል።

ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረጉት በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና የትምህርት ባለሙያዎች የሙያ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት ዳይሬክቶሬት የሙያ ፍቃድ ባለሙያ አቶ ሺፈራው ከፍያለው እንደሚገልፁት በሐምሌ 2014 ዓ.ም ወር በተደረገ አዲስ አደረጃጀት ምክንያት ይህ ዘርፍ ወደ "የትምህርት ጥራትና ሥልጠና ባለሥልጣን" ይሄዳል በሚል ተዘሏል። ከሥራው አስፈላጊነትና በስህተት መዘለሉ አኳያ እንደገና እንዴት መቀጠል እንዳለበት ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።

ከሌሎች፣ ልምድ ከተወሰደባቸው ሀገራት (ኢንዶኔዥያ፣ አውስትራሊያ፣ ፊሊፒንስ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጄሪያ፣ በቅርብ ጀምረው ውጤታማ የሆኑትን ዓረብ ኤምሬትስ ወዘተ) መረዳት የተቻለውም ይህንኑ ሲሆን፤ የሙያ ፍቃድ መስጠትና ማደስ ለትውልዱ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ እንዲሆን የላቀ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

እንደ አቶ ሺፈራው ማብራሪያ፣ ከእነዚህ ሀገራት ልምድ በመነሳትና ጉዳዩን ከሀገራችን አኳያ በመቃኘት ትምህርት ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም ምዘናውን የሰጠ ሲሆን፣ ከተገኘው ውጤት መረዳት እንደ ተቻለውም ከአጠቃላይ፣ ምዘናውን ከወሰዱት መምህራን መካከል




24 ነጥብ 2 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው መመዘኛውን በማለፍ የሙያ ፍቃድ ያገኙት።

በአሁኑ ግዜም መምህራኑ ምዘናውን እየተቀበሉ ሲሆን እንደውም ከክልሎች እየደወሉ 'ለምን አትፈትኑንም?' የሚል ጥያቄን እያነሱ ይገኛሉ። በተለይ አንዳንድ ክልሎች አንዳንድ ሥራዎች ሲኖሩ እድሉን በቅድሚያ የሚሰጡት የሙያ ፍቃድ ሰርተፊኬት ላላቸው መምህራን በመሆኑ ብዙዎች ያንን እድል ለማግኘት ምዘናውን ለመውሰድ ይፈልጋሉ። በመሆኑም ምዘናው እየተለመደና እየተፈለገ መጥቷል።

ከሌሎች ሀገራት፣ በተለይም ልምድ ከተወሰደባቸው ሀገራት አንዳንዶቹ ምዘናውን ላለፉ መምህራን 100 ከመቶ የደመወዝ ጭማሪ (ለምሳሌ 5ሺህ ብር ከሆነ ደመወዙ 10ሺህ) ስለሚያደርጉ ምዘናው በጣም ተፈላጊ ነው። ይህም አንድ መምህር በሚቀጥለው ዓመት ምዘናውን ካላለፈ የተጨመረለት ደመወዝ ይቀነስበታል ማለት ነው። በመሆኑም፣ ጭማሪውን ደመወዝ ላለማጣት መምህሩ በከፍተኛ ደረጃ ተዘጋጅቶ ምዘናውን የመውሰድ ፍላጎት አለው። ይህ ዝግጅት ደግሞ ለመምህሩ ብቻም ሳይሆን አጠቃላይ የመማር-ማስተማር ሥራው ላይ የሚኖረው መልካም ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም። በኢትዮጵያም ማበረታቻና ይህን የሚያሳይ አሠራር ቢዘረጋ ጥሩ ነው።

እንደ አቶ ሺፈራው አስተያየት በኢትዮጵያ ምዘናው እንጂ ተግባራዊ የተደረገው ምዘናውን ባለፉና ባላለፉት መምህራን መካከል ምንም አይነት መለያ የለም። ሁለቱም ማስተማሩን ይቀጥላሉ። ያላለፉት "ምን ይቀርብኛል" በሚልም ዝግጅት ሲያደርጉ አይታዩም። በመሆኑም ይህ ሊታሰብበት ይገባል።

እንደሀገር ሲታይ የመምህራን እጥረት አለ። ከዚህ አንፃር መመዘኛውን ወስደው ያለፉም የወደቁም ሥራቸውን ይቀጥላሉ። ይህ እንዲሆን የተደረገው የመምህራን እጥረት በፈጠረው ችግር እንጂ ተገቢ ሆኖ አይደለም። ያላለፈ መምህር ለተጨማሪ አቅም ግንባታ ወደ ሥልጠና መሄድ ያለበት። ከዛ አቅሙን ገንብቶ ሲመጣ የማስተማር ሥራውን መቀጠል ይችላል። ነገር ግን በዚህ መሠረት አይደለም እየተሄደ ያለው። ምክንያቱ ደግሞ የመምህራን እጥረት ጉዳይ ነው። ወደ ፊት ግን ወደዛ ነው መኬድ ያለበት።

በአዲስ አበባ ከተማ የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን አማካኝነት ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የመምህራን የሙያ ብቃት ምዘና፤ እንዲሁም፣ የመምህራን፣ የሱፐርቫይዘሮች እና ርዕሰ መምህራን የሥራ ምዘና ውጤቱ (JEG) እየተሰጠ ይገኛል። ተፈታኞችም ሁለት አይነት ፈተናዎችን፣ ማለትም የጽሑፍ ፈተና (80 ከመቶ) እና የማህደረ ተግባር ፈተና (20 ከመቶ) እንዲሁም የጽሑፍ ፈተናውን 62 ነጥብ 5 እና ከዛ በላይ ያመጡ ተመዛኞች የማህደረ ተግባር ፈተናውን እንደሚወስዱ ባለሥልጣኑ በወቅቱ መግለፁ ይታወቃል።

በዚሁ መሠረትም፣ በ2014 ዓ.ም በአዲስ አበባ የሙያ ብቃት ምዘና ከወሰዱ 1ሺህ 835 መምራን መካከል 1ሺህ 600ዎቹ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ማግኘት ችለዋል። ከዚሁ ጎን ለጎን የብቃት ምዘናውን እንዲወስዱ ባይገደዱም የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የሌላቸው መምህራን ማስተማር እንደማይችሉ መመሪያው ደንግጓል።

ከላይ አቶ ሺፈራው ከሰጡት አስተያየት መረዳት እንደሚቻለው በትምህርት ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ የተመዘገበው ውጤት ከተመዘኑት የትምህርት ቤት መምህራንና የትምህርት አመራሮች መካከል ያለፉት 24 ነጥብ 2 ከመቶ ብቻ ናቸው። ሌሎቹ ምዘናውን ማለፍ አልቻሉም።

ይሁንና በዚህ ምዘና ውጤት ተገኝቷል። መምህራኖቻችን እና የትምህርት አመራሮቻችን በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉና ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። በሚደረገው የክትትል (ሱፐርቪዥን) ሥራ የብቃት መመዘኛ የወሰዱ መምህራንና የትምህርት አስተዳደር ባለሙያዎች ያሉባቸው ትምህርት ቤቶች የተሻለ አፈፃፀም አሳይተዋል። ምዘናው ይህ አሠራር ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑ የታየበትና ለትምህርት ጥራት እውን መሆን አስፈላጊ እንደሆነ ማረጋገጫ ሰጥቷል።

በመምህራን ምዘና ላይ የታየው ውጤት በተማሪዎች ላይም ተንፀባርቋል። በ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ብዙ ተማሪዎች እንደወደቁ ሁሉ በመምህራን ምዘናም በርካታ መምህራን ወድቀዋል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከነዚህ ውስጥ የመምህራኖች በበቂ ሁኔታ ለምዘናው አለመዘጋጀት አንዱ ነው። የምዘናው ጥራት የተዋጣለት አለመሆንም እንደሁለተኛ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል።

ምዘናውን ያለፉ መምህራንን የሚያበረታታ ሽልማትም ሆነ ሌላ እንዲያገኙ የሚያደርግ አሠራር ገና አልተዘረጋም። ምናልባት «ባልፍም ብወድቅም ምን ይቀርብኛል» የሚል ነገር በመምህራኖች በኩል ሊኖር ይችላል። ከዚህ አኳያ ያለፉትን ሊያበረታታ የሚችል አሠራር ቢዘረጋ ጥሩ ይሆናል።

24 ነጥብ 2 ከመቶ ብቻ መምህራን ማለፋቸውና የአብዛኛው መውደቅ ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው በተማሪዎች ውጤት ላይ የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል። የመምህሩ ብቃት ማነስ ጎልቶ መታየቱ፣ መውጣቱ አይቀርም። ውጤቱም ሲታይ ከላይ ተመጋጋቢ ሆኗል። ይህ ደግሞ የሚያሳየው አስቀድሞ በመምህራን ላይ መሥራት ተማሪ ላይ መሥራት መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም የመምህራን ብቃት መጠበቅ፣ መኖርና መረጋገጥ አለበት። መምህራን ከመንግሥት የሚጠብቁት ነገር እንደ ሀገሪቱ አቅምና ሁኔታ ሊሟላላቸው ይገባል።

አቶ ሽፈራው እንደሚናገሩት ተመራቂ መምህራንን መመዘንን በተመለከተ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከአውስትራሊያ የተለየ አካሄድ ትከተላለች። አውስትራሊያ «በተቋሞቼ አቅም አምናለሁ፤ ተቋሞቼ በሚገባ መምህራንን አሠልጥነው እንደሚያወጡ አውቃለሁ» ትላለች። ስለዚህ የአውስትራሊያ መምህራን ተመርቀው ሲወጡ። ወይም ወደ መምህርነት ሙያ ሲቀላቀሉ አይመዘኑም። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ግን መምህራን ተመርቀው ሲወጡ ይመዘናሉ።

ይህ ሊሆን የቻለው በአፕላይድ ተመርቀው፤ ለተጨማሪ አንድ ዓመት የማስተማር ሥነ-ዘዴን (ፔዳጎጂ) ተምረው የጨረሱት ተፈትነው ምዘናውን ማለፍ ባለመቻላቸው ነው። ይህ ውጤት ለመምህራን ኮሌጆችና ለሚመለከታቸው ሁሉ ተሰጥቷል። ውጤቱም ብዙ ነገር አስተምሯል።

ሦስት አራተኛው መምህር ምዘናውን ማለፍ አለመቻሉ የትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ ብቃቱ ያልረጋገጠ መምህር ከተበራከተ ለዚህ ትልቁን ሚና የተጫወተው የማይጨበጠው እና በግብታዊነት የሚቀያየረው የመም ህራን ሥልጠና ሥርዓት መሆኑ የአንዳንዶች እምነት ነው።

ኤፍሬም ተክለያዕቆብ የተባሉ ሰው በ2018 /እ.አ.አ./ እንዳሰፈሩት፣ የ2007 ዓ.ም የትምህርት ሚኒስቴር ዓመታዊ አብስትራክት (ጭማቂ) እንደሚያሳየው በሀገሪቱ ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ትምህርት ድረስ 497 ሺህ 735 መምህራን የነበሩ ሲሆን፤ ከእነዚህ መካከል 429 ሺህ 288፣ ወይንም 86 ነጥብ 24 ከመቶው እድሜያቸው ከ 40 ዓመት በታች ነው። እነዚህ መምህራን ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሥራ ላይ ያለው የትምህርት ፖሊሲ ውጤት ናቸው። በመሆኑም፣ የምዘናው ውጤት ወደ ወደኋላ በመመለስ የመምህራን ቅበላን፣ ሥልጠናን እንዲሁም ተከታታይ ማብቃትን እና ማበረታቻ ሥርዓትን ለመፈተሽ መነሻ ሐሳብ ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል።

ያነጋገርናቸው የጉዳዩ ባለቤት እንደሚሉት ምዘናው ባጠቃላይ የትምህርት ማዕቀፉ አካል እንጂ ብቻውን ተነጥሎ ሊታይ የሚገባው አይደለም። በመሆኑም በእሱ ብቻ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ መድረስ አይገባም። ሌሎች በርካታ መመዘኛዎችም አሉ። የእነሱ ሁሉ ድምር ነው የመምህሩ የመጨረሻ ሙያዊ ማንነት መገለጫ። የምዘና ውጤቱ ወደ ኋላ በመመለስ አሠራሮች ሁሉ እንዲፈተሹ እድል መፍጠር አለበት።

መምህራንን የመመዘኑ ተግባር አስፈላጊነቱ የሚታመንበትና አይቀሬ ከሆነ በተጠናከረ ተቋማዊ አሠራር መደገፍ እንዳለበት የማንም እምነት ስለመሆኑ መጠራጠር አይቻልም። ይህ እውነት ከሆነ፣ የመመዘንና ለተመዛኙ ግብረ-መልስን በተገቢው የመስጠት ተቋማዊ ብቃት ሊኖር ይገባል። የመምህራን ምዘና ውጤታማነት በመዛኙም ሆነ በተመዛኙ በኩል ተገቢ የሆነ ብቃትና ክህሎት ላይ የተመሠረተ መሆኑም ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

በሌላ አነጋገር «የምዘናው ውጤት የተመዛኙን ክፍተት ብቻ ሳይሆን የመዛኙም ችግር ነፀብራቅ ነው» ከሚለው የባለሙያዎች አስተያየት ጋርም አለመስማማት አይቻልም። በመሆኑም፣ እንደ አንድ የሚኒስቴሩ የምዘናና የሙያ ፍቃድ አሰጣጥ ዘርፍ ተዋቅሮ ሥራውን ሲሠራ የነበረው እንደ ገና በተጠናከረ መልኩ ተመልሶ ሥራውን በባለቤትነት ሊይዘውና ሊያከናውነው ይገባል። የትምህርት ጥራትን የማስጠበቁ ተግባርም መጠናከር ይኖርበታል።

# ወቅታዊ

# «ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የያዘችን ሀገር ያለወደብ ትቀጥል ማለት ኢ-ፍትሐዊነት ነው»

- ረዳት ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካርያ

እፀገነት አክሊሉ

ኢትዮጵያ የባሕር በር ከሌላቸው አገሮች መካከል አንዷ ነች። አገሪቱ ያለ ባሕር በር መኖር ከጀመረች ከሩብ ክፍለ ዘመን በላይ ተቆጥሯል። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ስትሄድ የአሰብንና የምፅዋን ወደቦች ይዛ በመሄዷ ወደብ አልባ አገር ሆናለች።

የባሕር በር ወይም ወደብ ለአንድ አገር ኢኮኖሚ ወሳኝ ከመሆኑ ባሻገር ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ መሆኑን ባለሙያዎች ይናገራሉ። በአሁኑ ወቅት ጂቡቲ ከአራት በላይ ወደቦች አሏት። ይህች ትንሽ አገር ተፈላጊነቷም ከአውሮፓ እስከ አሜሪካ እንዲሁም ከአሜሪካ እስከ እስያ ድረስ ደርሷል። የተወሰኑ አገሮች ቻይናን ጨምሮ በአሁኑ ወቅት በዚች ትንሽ አገር ወታደራዊ ቤዝ ገንብተዋል። እነዚህ አገሮች ወደዚች ትንሽ አገር መጥተው ወታደራዊ ቤዝ እንዲኖራቸው ካስፈለጋቸው ምክንያቶች መካከል የአካባቢው ተፈላጊነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ እንደሆነም ባለሙያዎች ያብራራሉ፡፡

በሌላ በኩልም ሳውዲ ዓረቢያ ከአሰብ ወደብ ከፊሉን ከኤርትራ በሊዝ ገዝታ ለብዙ ዓመታት ለማስተዳደር ፈቃድ አግኝታለች። በአሁኑ ወቅት የአሰብና የምፅዋ ወደቦች የዓረብ አገሮች በተደጋጋሚ ጊዜ ወደዚህ አካባቢ ሲሄዱና ወታደራዊ ሠፈር ሲያቋቁሙ ታይቷል። በአሁኑ ወቅት የጂቡቲ ወደቦች በሁለት ሳምንት የሚያንቀሳቅሱትን ያህል በዓመት ማንቀሳቀስ እንደማይችሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አሁንም ድረስ ግን ተፈላጊ መሆናቸው የማይካድ ነው፡፡

የጂቡቲን ወደቦች ኢትዮጵያ፣ ኬንያና ሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ አገሮች ይጠቀሙበታል። እነዚህ አገሮች የጂቡቲ ወደቦችን የኢትዮጵያን ያህል የሚጠቀሙ ባይሆንም፣ በአካባቢው ላይ ያላቸው ፍላጎትና ዝንባሌ ግን ከፍተኛ ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓመት ለወደብ ኪራይ ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ለጂቡቲ እንደምትከፍል መረጃዎች ያመለክታሉ። ከ90 በመቶ በላይ የሚሆነውን ወጪና ገቢ ንግዷን የምታካሂደውም በጂቡቲ ወደቦች አማካይነት ነው። የጂቡቲ መንግሥት ከቻይና ባገኘው ሦስት መቶ ሚሊዮን ዶላር ድጋፍም አዳዲስ ወደቦችን እየገነባና እያስፋፋ ሲሆን የወደብ ማስፋፋት ፕሮጀክቱ በዋናነት ታሳቢ አድርጎ የሚንቀሳቀሰውም ኢትዮጵያን ነው፡፡

በሌላ በኩል ንብረትነቱ የሶማሌላንድ የሆነው የበርበራ ወደብ ተፈላጊነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል። ኢትዮጵያ ይህን ወደብ የማስተዳደር 19 በመቶ ሥልጣን ቢኖራትም፣ በዋናነት የሚተዳደረው ግን በተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ መንግሥት ነው። ሶማሌላንድ 35 በመቶ፣ ኢትዮጵያ 19 በመቶ ድርሻ ያላቸው ሲሆን፣ 46 በመቶ ወደቡን የማስተዳደር ሥልጣን የኤምሬትስ መንግሥት ነው፡፡

በዚህ የአፍሪካ ክፍል በተለይም በቀይ ባሕር አካባቢ ያለውን የባሕር በር በቅርብ ሆኖ ለመከታተል፣ እንዲሁም አማራጭ ወደብ ለማግኘት በማለት የተለያዩ ሀገሮች በእነዚህ ወደቦች ላይ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡ ኢትዮጵያም በበኩሏ የባሕር በር የሌላት አገር ከመሆኗ አንፃር የጂቡቲ ወደቦችን በመከራየት የገቢና ወጪ ንግድ እንቅስቃሴዋን ስታካሂድ ቆይታለች።

አገሮች የወደቦች ሽሚያ በሚመስል ውድድር ውስጥ በመግባት የባሕር በርና ወደብ ወዳላቸው ሀገራት ፊታቸውን እያዞሩ ነው። ኢትዮጵያም በአሁኑ ወቅት የጅቡቲ ወደብን የወጪና ገቢ ንግዷን ለማሳለጥ አብዝታ እየተጠቀመችበት ነው፡፡

የጂቡቲ መንግሥት እንደሚለው በዓመት 35 ሺ የተለያዩ አገሮች መርከቦች በጅቡቲ በኩል ያልፋሉ። በዚህ የተነሳ ጂቡቲ በዓመት በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ታገኛለች። በእነዚህ ወደቦች በዋናነት ኢትዮጵያ የምትጠቀም ቢሆንም ኡጋንዳና ኬንያም ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡


የሶማሌላንድ የበርበራ ወደብም ዓለም አቀፍ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን ይህ አካባቢ ከወደብ አገልግሎት ባሻገር ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች እንዳሉት ይነገራል። ለአብነት ያህልም በአካባቢው የኤምሬትስና የኳታር ወታደሮች ይገኛሉ። በተለይ የገልፍ አገሮች ይህንን አካባቢ እንደሚፈልጉት ይነገራል። በዚህም የተነሳ በአካባቢው እየተፈጠረ ያለውን ወታደራዊ አሰላለፍና ጫና በቅርብ ሆኖ ለመከታተልና አካባቢውን አሳልፎ ላለመስጠት፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ፊታቸውን ወደዚያ እንዳዞሩ ባለሙያዎች ሲናገሩ ይሰማል፡፡

ነገር ግን ኢትዮጵያ ለአያሌ ዓመታት ታስተዳድረው በነበረው የቀይ ባሕርና የባሕር በሮቿ ግዛቶችም ከላይ ከተጠቀሱት ሀገራት ጋር የዝሆን ጥርስ የቅመማ ቅመም ምርቶችን የሙጫ ተክሎችን እንዲሁም ሌሎች ወጪና ገቢ ሸቀጦችን አልባሳት ሽቶና ጌጣጌጦችን በመላክና ወደሀገር ውስጥ በማስገባት የተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴ ታካሂድ እንደነበርም የአባቶቻችን የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ይህ ብቻም አይደለም የቀይ ባሕር ወደብን እንደ አሸዋ ትናኝበት በነበረበት ጊዜ ከየመን እስከ ሕንድ ከሶሪያ እስከ እስራኤል ከሳውዲ ዓረቢያ እስከ ግብጽ ከቻይና እስከ አውሮፓና ኤዢያ ድረስ ጠንካራ የመንግሥታት ግንኙነትን በመፍጠር የልዕለ ኃያልነት አስፈሪነቷን ለዓመታት እንደቆየችበት የሀገሪቱ የዲፕሎማሲ ታሪክ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው እውነት ነው። ይህም በዘመኑ በቀይ ባሕር ቀጠና ከፍ ያለ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ብልጽግናን ካነገሡ ሀገራት ቀዳሚዋና ፋና ወጊ ሲያስብላት ቆይቷል።

በዚህ ገናናነቷ ዓለምን ሲቀይር የሚችል አቅምን መፍጠርን እንደቻለችም በብዙ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች ሳይቀር ዛሬም ድረስ የምትታወስ ሀገር ስትሆን የዚህ ታላቅነቷ ምስጢር ሲገለጽ ደግሞ ግርማቸው ከሩቅ የሚያስፈራ በጥበብም ቀድመው የነቁ የበቁ መሪዎችና በሥነ ምግባር በሀገር መውደድና አርቆ በማሰብ ውስጥ የነበሩ ተመሪ ሕዝቦችም የነበሯት ሀገር እንደነበረች የሚያሳይ ነው። በአንጻሩ የአገሪቱን የቀዳሚነት መንገድ ይዞ ካለመዝለቅ የመነጩ ክስተቶችን ያስተናገደችው ኢትዮጵያ በተለይም ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት በኋላ የዓለም ነባራዊ ሁኔታ መቀየር በራሷ በሀገሪቱም የመሪዎች መለዋወጥ ምክንያት አገሪቱን ካለወደብ በሚያስቀር ውል ኤርትሪያ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል ሆነ። ይህ መሆኑ ደግሞ የሀገሪቱን ፖለቲካዊ ወታደራዊና ዲፕሎማሲያዊ ኩነቶች በመቀያየር ሀገሪቱን ወደብ አልባ ከማድረጉም ባሻገር ለዘመናት የቀይ ባሕርና የበርካታ ወደቦች ባለቤት የነበረች ኃያልና ክቡር ሀገር አሁን ላይ ወደኋላቀርነት ድህነት የገባችበት ሁኔታ ነው ያለው ባሕርና ከኤደን ባሕረሰላጤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነቷ ውጪ እንድትሆን አስገድዷታል።

በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ ወደብ አልባ ሀገር በመሆኗ በወጪ ገቢ ምርቷ ላይ የሌላ ሀገር ጥገኛ እንድትሆን አስገድዷታል። ይህም ለራሷ ታውለው የነበረውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ በማቀጨጭ በኢኮኖሚዋ ላይ እድገት እንዳይመዘገብ የፊጥኝ አስሯታል። ከቀይ ባሕር በ60 ኪሎ ሜትርና ከሕንድ ውቂያኖስ በ2 መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ቢሆንም እነዚህን አካባቢዎች ተጠቅማ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን እንዳታደርግ የማግለል ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። የአፍሪካውያን የነፃነት ተምሳሌት የሆነችው ኢትዮጵያ በጥንታዊው ሥልጣኔዋና ገናናነቷ ከቀይ ባሕር እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የነበራትን ኃያልነት መርምሮ ዘመኑን ታሳቢ ባደረገ ዓለም አቀፍ የወደብ አጠቃቀም መርሕን ፈትሾ የምሥራቅ አፍሪካና የአፍሪካ ፖለቲካዊ አካሄድ ተረድቶ በሰላማዊ ንግግርና ምክክር የኢትዮጵያም የወደብ መጠቀም መብት ሲከበር የሚገባበት ወቅት ላይ ነን።

የአዲስ ዘመን ዝግጅት ክፍልም በዚህና መሰል ጉዳዮች ዙሪያ ከረዳት ፕሮፌሰር አሕመድ ዘካሪያ ጋር ቆይታ አድርጓል።



ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

**በዘመኑ በቀይ ባሕር ቀጣና ከፍ ያለ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ብልጽግናን ካነገሡ ሀገራት ቀዳሚዋና ፋና ወጊ ሲያስብላት ቆይቷል**

**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ ኢትዮጵያ የምትገኝበትን የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣናን እንዴት ይገልጹታል?**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፡-** የአፍሪካ ቀንድ ብዙ ታሪክ ያለው ተዓምራት የሚመስሉ ነገሮች ሁሉ የተከናወኑበት አካባቢ ነው። በተለይም ኢትዮጵያ ደግሞ የሰው ዘር መገኛ ከመሆኗ የተነሳም ብዙ ታሪክ ያላት ናት። የምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ በብዙ ችግር የተተበተበ ነው። በአካባቢው ሁለት ዓይነት እረፍት የለሽ ተቀናቃኝ ሁኔታዎች አሉ። ይህ ደግሞ ይበልጥ ኢትዮጵያን ነው የሚመለከተው። በኢትዮጵያ ላይ አንደኛ ታሪካዊ ተቀናቃኞች፤ ሁለተኛ ደግሞ ተፈጥሯዊ ተቀናቃኞች አሉባት። ታሪካዊ ተቀናቃኝ የምንላቸው ሰፊና ረጅም ታሪክ ያላቸው ናቸው። እነዚህ በታሪክና በባሕል የሚቀናቀኗት ናቸው። ተፈጥሯዊ ተቀናቃኞቿ ደግሞ በሃብት የሚቀናቀኑ ናቸው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣናው በተለይም በቀይ ባሕር አካባቢ ያለውን የኢትዮጵያ ሚና እንዴት ይገለጻል?**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፡-** ብዙ ጊዜ የውሃ እንቅስቃሴዎች የሥልጣኔ ምልክቶች ናቸው። ይህ ደግሞ በትልልቅ ወንዞችም ሆነ በባሕር ጠረፎች ላይ የሚገለጽ ነው። እስከ ዛሬ ድረስም የታዩት ሥልጣኔዎች በሙሉ በዚህ ዙሪያ ናቸው። ለምሳሌ የሰው ልጅ በእግሩ ፤በፈረስ ፤በበቅሎ በግመል አለፍ ሲልም በመኪና በባቡር በአውሮፕላን ይንቀሳቀሳል። ነገር ግን በመርከብ አማካይነት በባሕር ላይ የሚደረግ እንቅስቃሴ ትልቅ ቦታ የሚይዝ ነው። በተለይም በትልልቅ ንግድ ሥርዓት እንዲሁም ሀገራዊ ጥቅሙ የመርከብን ያህል አገልግሎት የሰጠ የለም። እስከ ዛሬ ድረስ ግን ኢኮኖሚያችን በተወሰኑ ነገሮች ላይ የተገደበ ስለነበር ባሕር ቢኖረንም ባይኖረንም

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# «ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የያዘችን ሀገር...

ከ ገጽ 9 የዞረ

የመርከብ ጥቅም ብዙ ሳይሰማን ቆይቷል። ዛሬ ላይ ግን አንደ ሀገር የሕዝብ ቁጥራችን በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ ይህንን ተከትሎም የፍላጎት እቃዎች መብዛታቸው ከሁሉም በላይ ደግሞ እያሳየን ያለነው ኢኮኖሚያዊ እድገት መርከብን እንድናማትር አድርጎናል ማለት ይቻላል።

ይህ መርከብን ማማተራችን ደግሞ ማሳረፊያውን ወደብ እንድንፈልግ ምክንያት እየሆነን ነው። በመሠረቱ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት በነበረችበት ጊዜ ምርቷ በሙሉ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚከፋፈል ነበር። ለዘመናት የቀይ ባሕርና የበርካታ ወደቦች ባለቤት የነበረች ሀገር ነበረች ። አሁን ላይ ወደኋላቀርነት ድህነት የገባችበት ሁኔታ ያሳዝናል።

ይህም በዘመኑ በቀይ ባሕር ቀጣና ከፍ ያለ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ብልጽግናን ካነገሱ ሀገራት ቀዳሚዋና ፋና ወጊ ሲያስብላት ቆይቷል። በዚህ ገናናነቷ ዓለምን ሊቀይር የሚችል አቅምን መፍጠርን እንደቻለችም በብዙ የውጭ አገር ዲፕሎማቶች ሳይቀር ዛሬም ድረስ የምትታወስ ሀገር ስትሆን የዚህ ታላቅነቷ ምስጢር ሲገለጽ ደግሞ የወደብ ባለቤትነቷ ነው።

የቀይ ባሕር ታሪክ በጣም ሰፊ ነው፤ ከክርስትና እስልምና አይሁድ ጋር በጣም ቁርኝት ያለው ነው። ከዛም በፊት የዓባይ ሸለቆን ሥልጣኔ ያማከለ ቦታ ከመሆኑ አንጻር በታሪክ ሂደትም ብዙ የምንናገርለት ሂደት አለ። በተለይም ኢትዮጵያ የቀይ ባሕርን የንግድ እንቅስቃሴ በመቆጣጠሯ ምክንያት በወቅቱ የአክሱም ሥልጣኔ እንዲያብብ ምክንያት ሆኗል። በወቅቱም በዓለም ላይ ከነበሩት ሥልጣኔዎች አንዱ ሆኖ ለመውጣቱም ምክንያቱ የባሕሩ ንግድ ነው።

**አዲስ ዘመን፦እንዴት በቀይ ባሕር ላይ የነበራትን የበላይነት ልታጣ ቻለች**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፦** ኢትዮጵያ የባሕር በሯን ለመጀመሪያ ጊዜ ያጣችው በቅኝ ግዛት (በኮሎኒያል) ጊዜ ነው። የአፍሪካ ቀንድ የበርካታ ኃያላን ሀገራትን ትኩረት የሚስብ ስትራቴጂክ ስፍራ ነው። በተለይም አካባቢው በቀይ ባሕር እና በናይል ውሃ ተፋሰስ መሐል መገኘቱ የበርካታ ሀገራትን ቀልብ ሊስብ ችሏል። የቀይ ባሕር እና የናይል ፖለቲካ የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን በማወዳጀትም ሆነ በማራራቅ ከፍተኛ ሚና ያለውን ያህል አካባቢውን በቁጥጥራቸው ለማዋል ሕልም ያላቸውም ሀገራት የሚራኮቱበት ነው።


ቀይ ባሕር በተለይ ከስዊዝ ካናል መከፈት ጋር ተያይዞ የዓለም የንግድ ኮሪደር ለመሆን ችሏል። ቀይ ባሕርን የመቆጣጠር ፍላጎት የዓለም ኃያልን ሀገራት ሁሉ ምኞት ነው። እነዚህ ሀገራት ኢትዮጵያ እንዳትቀናቀናቸው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ከአካባቢው እንድትርቅ አድርገዋታል።

የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና በአጠቃላይ 8 አገ ሮች አሉ። እነዚህ አገሮችም በሚጠቅማቸው በሚያዋጣቸው አካሄድ ላይ እየተመካከሩ ያለውን ችግር ለመፍታት በቂ እውቀትም ችሎታም ያላቸው ናቸው። ኢጋድ መጀመሪያ ሲቋቋም ዓላማው ረሀብንና ድርቅን መቋቋም ነበር። ነገር ግን ይህም ሌላኛው ድርቅ በመሆኑ የተፈጥሮ ሀብታችንን አብረን የምናለማበት የምንጠቀምበት ሁኔታ ሊመቻች ስለሚገባው ይህንንም አብሮ ማየት ሳያስፈልግ አይቀርም።

ኢትዮጵያም ለጎረቤቶቿ በሙሉ ውሃ ታቀብላለችና ይህንን የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ሂደቷን ደግሞ በባሕር ወደቡ በኩልም በማምጣት ከጎረቤቶቿ ጋር ተስማምታ መጠቀምን ማስቀደም ይገባታል።

ይህ እንዲሆን ደግሞ ምናልባትም ብዙ ምክክር ውይይት የሚያስፈልግ ሲሆን ይህንን ካደረግን ደግሞ ችግሩን ፈተን በጋራ ተጠቃሚነታችን እንደሚጠናከር አምናለሁ።

ወንድም እህቶቻችን አፋሮች የድንበር ጠባቂ ሆነው አገልግለውናል፤ አሁንም እያገለገሉን ነው።



ቀይ ባሕር በተለይ ከስዊዝ ካናል መከፈት ጋር ተያይዞ የዓለም የንግድ ኮሪደር ለመሆን ችሏል። ቀይ ባሕርን የመቆጣጠር ፍላጎት የዓለም ኃያልን ሀገራት ሁሉ ምኞት ነው። እነዚህ ሀገራት ኢትዮጵያ እንዳትቀናቀናቸው የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ከአካባቢው እንድትርቅ አድርገዋታል

የጠረፉ ንግድም በቀጥታ የሚያያዘው ከእነሱ ጋር ነው። ደገኛው ቆላ ውስጥ መኖር አይችልምና ሥልጣኔዎች ደግሞ በብዛት ያሉት ደጋው ላይ ነው፤ ቆላው ከአየር ንብረቱ የተነሳ ለመኖር ምቹ ስላልሆነ ሰፋ ያለ ሕዝብ ላይሰፍርበት ይችላል፤ በመሆኑም ደጋው ወደ ቆላ ወርዶ የሚነግድበት ሁኔታ ነበር፤ እስከአሁንም አለ። የወደቡ ጥያቄ በ16ተኛው ክፍለ ዘመን ኦቶማኖችና ቱርኮች ያደረጉት መራኮት አካባቢውን አናውጦት የነበረ ሲሆን እኛም ብዙ ጉዳቶችን አስተናግደናል። በዚህም ምፅዋንና ሌሎች ቦታዎችን እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ኦቶማኖች ይዘውት ነበር።

ከዛ ደግሞ ሲውዝ ካናል ሲከፈት መራኮቱ በረከተ። ሁሉም ቅኝ ገዢዎች የሚፈልጉት ቦታ ሆነ። በተለይም ሕንድን ቻይና አፍሪካ ላይ የሚያደርጉትን የንግድ አንቅስቃሴ በግማሽ ስላሳጠረላቸው በሂደት ደግሞ አካባቢው የነዳጅ ሀብት የሚተላለፍበት መሆኑ ተፈላጊነቱን ጨመረው። እዚህ ውስጥ ደግሞ የኢትዮጵያ ድርሻ አለና ቅኝ ገዢዎቹ በ19ኛው ክፍለ ዘመን ያደረጉት ደባ ጅቡቲንም ኤርትራንም ሱማሊያንም ከአፍሪካ ቀንድ በታተነው። የኢትዮጵያ የወደብ ድርሻዋም ራቀ።

ከፋሺስት ጦርነት በኋላ በነበረው ጊዜ ደግሞ ኤርትራ ወደእናት ሀገሯ ተመልሳ በሰላም እንኖር የነበረ ቢሆንም በየጊዜው የነበሩ መሪዎቻችን የማይሆን አይነት ውሳኔ ወስነው አሰብን አስወሰዱ።

ነገር ግን በወቅቱ አሰብን ልናስቀርበት የምንች ልበት ታሪካዊ ሕጋዊና ሌሎች ብዙ ነገሮች እያሉ የተሳሳተ ውሳኔ በመወሰናቸው ምክንያት ዛሬ የደረስንበት ደረጃ ላይ እንድንደርስ ምክንያት ሆኗል።

አሁንም ቢሆን ግን የኢትዮጵያ የባሕር በር ፍላጎት ወይም ጥያቄ በሰላምና በውይይት በምክክር ይፈታ ዘንድ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብታችንን በጋራ የምናለማው እንጂ የምንራኮትበት ሊሆን አይገባም።

አሁን ባለው ሁኔታ የሕዝብ ቁጥራችን ከ120 ሚሊዮን በላይ ደርሷል። ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የያዘችን ሀገር ያለወደብ ትቀጥል ማለት ኢ-ፍትሐዊነት ነው። ለቀጣናውም አስቸጋሪ ነው። በመሆኑም ይህንን ሰፊ መስመር በሰላም ለመጠቀም ውይይት ምክክር የምሑራን ሚና ከፍተኛ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ በአካባቢው ኢትዮጵያ ሚናዋ እየቀጨጨ መምጣቱ እንደሀገር ምን አሳጥቶናል?**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፦** ባለፉት ሠላሳና ምናምን ዓመታት ባሕር በር አልባ መሆናችን ስፍር ቁጥር የከሌለው ጉዳት አስከትሎብናል ያጣናቸው ነገሮችም ብዙ ናቸው። እንደ አገር ወጪ ገቢ ንግዳችን ተስተጓጉሏል፤ ወጪያችንም በጣም በዝቷል፤ እንደልባችን የጦር መሣሪያም ሆነ ሌሎች ነገሮችን ማስገባት ሳንችል ቀርተናል። ይህንን ችግር ለማስቀረት ጠቅላይ ሚኒስትሩም እንዳሉት በርካታ አማራጮችን ማየት ያስፈልገን ይሆናል። ለምሳሌ ወደብ አልባ ከሆኑ ጎረቤቶቻችን ጋር ወደብን በጋራ ማልማት፤ ኢትዮጵያ ከምታለማቸው መሠረተ ልማቶች ጥቂቱን ሰጥቶ ወደብ ማግኘት፤ የቦታ ቅይይር ማድረግና የመሳሰሉትን መጠቀም ይጠቀሳል። ይህንን ሁሉ ስናደርግ ሰላማዊ ሂደትን በመከተል ግን የመጀመሪያ አማራጫችን ማድረጉንም መዘንጋት አያስፈልግም።

በሌላ በኩል ግን ውስጣዊ ሰላም ማረጋገጥ የቅድሚያ ቅድሚያ ሊያገኝ የሚገባው ነገር ነው። ምን ጊዜም ቢሆን የሀገር ጉዳይ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ጥረት ማደረግ ከመንግሥትም ይሁን ከእኛ ከዜጎች የሚጠበቅ የቤት ሥራ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ የውስጥ ሰላምን ማረጋገጥ ይገባል። ሌላው ደግሞ በእያንዳንዱ ዜጋ ውስጥ የአገር ፍቅር ስሜት ዘልቆ ሊገባ ይገባል።

**አዲስ ዘመን፦ ከስውጡ ወዲህ በቀጣናው ላይ የኢትዮጵያን ሚና ለማጎልበት እየተሠራ ያለውን ሥራ እንዴት ይመለከቱታል ?**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፦** ጥሩ ነው መሪዎችም በብዛት ንግግሮችን እያደረጉ ነው፤ ምናልባት ሁሉም ነገር መስመር እስኪይዝ ድረስ አንዳንድ አስቸጋሪ ነገሮች መኖራቸው የማይቀር ነው። ለምሳሌ ሶማሊያና ኢትዮጵያ አንዳንድ ስምምነቶችን አድርገው ነበር፤ የራሱ የሆነ ድክመት የነበረበት ቢሆንም፤ ነገር ግን አሁን ደግሞ 8ቱንም የኢጋድ አባል ሀገራት በማወያየት ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በመሆኑም ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል የዓለምን ነባራዊ ሁኔታዎች እያዩም ውይይትና ምክክሮቹ በዛም መልክ እንዲሄዱ ማስቻል ወደውጤቱ ያቀርበናል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፦ ሰላማዊ አማራጮችን በመጠቀም የወደብ ባለቤትን ለማረጋገጥ የተወሰዱ ዓለማቀፋዊ ተሞክሮዎች ካሉ ቢያብራሩልን ?**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፦** የዓለም ተሞክሮ የሚያሳየን ሁሌም ቢሆን ሰጥቶ መቀበል ወሳኝ መሆኑን ነው። በመሆኑም የፖለቲካ ሂደቶቻችን ችግር የሚመዝ ሳይሆን ችግር ፈቺ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ በኢጋድ በኩል ያሉ አባል አገራት ቁጭ ብለው መወያየት መቻል ይኖርባቸዋል።

በመሠረቱ ሁሉም ቢሆኑ የውጭ ጫና ውስጥ ስለመሆናቸው እንገነዘባለን። ነገር ግን ውይይታቸውም እነሱን ታሳቢ ያደረገ አድርገው በአጠቃላይ ግን የራሳችንን ችግር ራሳችን እንፈታለን ብለው በአንድነት መቆምን መልመድ ይገባቸዋል።

ይህ ሳይሆን ቀርቶ ግን ከባልሽ ባሌ ይበልጣል አይነት ግብ ግብ ውስጥ ከተገባ ግን ሁኔታው በጣም አስቸጋሪ ነው የሚሆነው። በመሆኑም ደግሞ እለዋለሁ 8ቱ ሀገራት መሪዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሁኔታው ላይ እንዲወያይ መድረክ ማመቻቸትና መክፈት ይገባል። ይህንን ማድረግ ከተቻለና መሠረት ከተያዘ ማስማማቱ ብዙም ከባድ አይሆንም።

**አዲስ ዘመን፦ ስነበረን ጊዜ በጣም አመሰ ግናለሁ።**

**ረ/ፕሮፌሰር አሕመድ፦** እኔም አመሰግናለሁ

# ፋሽን

## አለባበስን ሙሉ የሚያደርጉ ጌጣጌጦች

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ስለ አለባበስ ውበት ስናነሳ እንደተጨማሪ መዋቢያ የሚያገለግሉት የጌጣጌጦች ጉዳይ መነሳቱ አይቀሬ ነው። በአለባበሳችን የቱንም ያህል ብንዘንጥ፤ ከአለባበሳችን ጋር አብሮ ሊሄድ የሚችል ጌጣጌጥ እስካልተጠቀምን ድረስ የሆነ የጎደለ ነገር ያለ ያህል ይሰማናል። የተለያዩ በዓላት እና የተለያዩ ፕሮግራሞች ሲኖሩን አምረን፣ ተውበንና ደምቀን ለመገኘት ለአለባበሳችን ቅድሚያ ሰጥተን እንደምንጠነቀቅ ሁሉ ከአለባበሳችን ጋር አብረው ሊሄዱ የሚችሉ፤ ጌጣጌጦች መምረጥ ይጠበቅብናል።

የአለባበሳችን ውበት የሚለካው ከምናጠልቀው ጫማ፣ ከምናደርጋቸው የጆሮ፣ የአንገት፣ የእጅ፣ የእግር እና የፀጉር ጌጦች ጋር አብሮ ታይቶና ተመዝኖ ነው። እገሊት እኮ! የለበሰችው ልብስ ከነጌጣጌጦቹ እጅግ ውብ አድርጓታል። አቤት ያጠለቀችው የጆሮ፣ የአንገትና ወዘተ. ጌጥ እንዴት ያምራል፤ እጅግ ውብ ነው! ቁንጅት ብላለች! እያልን አድናቆታችንን የምንቸረው።

ጌጣጌጦች እንደ ተጨማሪ መዋቢያ የሚጠለቁ(የሚደረጉ) ናቸው። እነዚህም የአንገት ሀብል፣ የእጅ አምባር፣ የጣት ቀለበት፣ የጆሮ ጉትቻና የእግር አልቦ በመባል ይታወቃሉ። የሰዎች ጌጣጌጦች ለበርካታ ዓመታት ለመዋቢያነትና ለማጌጫነት ሲጠቀሙባቸው መቆየታቸው የሚታወስ ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ጌጣጌጦች ለመዋቢያ ከሚሰጡት አገልግሎት በተጨማሪ የሀብት መለኪያና መገለጫ ተደርገው ይወሰዱ እንደነበር ይነገራል።

ጌጣጌጦች እንደየጊዜው ስሪታቸው ሆነ አይነታቸው ይለያያል። በተለይ ዘመናዊ የአለባበስ ሥርዓት የሚከተሉት የፋሽኑን ዓለም ሰዎች ስንመለከት እንደሚለበሰው ልብስ አይነት የሚለበሱት ጌጦችም ሆነ ስሪታቸው ሳይቀር ዘመነኛና ቄንጠኛ ናቸው። መዋቢያ አይነታቸውና ስሪታቸው ብቻ ሳይሆን ለመዋብና ለማጌጥ የሚጠቀሙባቸው የሰውነት ክፍሎች ጭምር ሳይቀር የተለዩ ናቸው።

መዋቢያ ጌጣጌጦች እንደየ ሀገሩ ባሕል ከተለያዩ ቁሳቁሶች የሚሠሩ ሲሆን ቀደም ሲል ለጌጥነት የሚውሉት ጌጣጌጦች አብዛኞቹ ከወርቅ፣ ከአልማዝ፣ እና ከብር ይሠራሉ። አሁን ላይ ግን ከእነዚህ በተጨማሪ የከበሩት ድንጋዮች፣ ከጨሌ፣ ከብረታ ብረት፣ እና መሰል ቁሳቁሶች የሚሠሩ ሲሆን፤ እነዚህ ጌጣጌጦችም የተለያየ ይዘት፣ ቅርጽና ቀለም አላቸው። ጌጣጌጦቹ ከዘመኑ ጋር እየዘመኑና አሠራራቸውም እየተሻሻለ የሚሄዱ ሲሆኑ ዛሬ ላይ ፋሽን ሆኖ አብዛኛው ሰው ሲያጌጥበት የነበረው ጌጥ ከትንሽ ጊዜ በኋላ ፋሽንነቱ ቀርቶ ሌላ አይነት ጌጥ በቦታ ይተካና የተሻለ የሚያምርና ውብ ፋሽን ሆኖ ብቅ ይላል፡፡

እነዚህ እንደ ተጨማሪ መዋቢያነት የሚያገለግሉት እጅግ ተፈላጊ የሆኑትን ጌጣጌጦች በግለሰቦችም ሆነ በተቋማት ይመረታሉ። ምርቶቹም ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ገበያም የሚቀርብበት ሁኔታም እንዳለ ይስተዋላል።



**የሰላማዊት የጌጣጌጥ ምርቶች**

ጌጣጌጦችን ከሚያመርቱት ተቋማት የእንጦጦ ዕደ ጥበብ ማዕከል አንዱ ነው። የማዕከሉ የማርኬቲንግ ባለሙያዋ ወጣት ይዲዲያ ሰለሞን እንደምትለው፤ በማዕከሉ የአንገት፣ የጆሮ፣ የእጅ፣ የእግርና ጸጉር ላይ የሚጠለቁ (የሚደረጉ) የተለያዩ ጌጣጌጦች ይመርታሉ። ጌጣጌጦቹ ባሕላዊ ይዘት ያላቸው ሲሆን፤ ለሰርግ፣ ለምርቃት፣ ለተለያዩ ፕሮግራሞችና ለመሰል ሰዎች ለሚፈልጓቸው ፕሮግራሞች ሁሉ ይውላሉ። ከየትኛውም አይነት አለባበስ ጋር አብረው የሚሄዱ ስለሆኑ ለመዋቢያና ለመዘነጫ ያገለግላሉ፡፡

እነዚህ ጌጣጌጦች ለመዋቢያነትና ለመዘነጫነት የሚያገለግሉ እንደመሆናቸው መጠን እንዲያምሩና ውብ እንዲሆኑ ተደርገው የሚሠሩ ናቸው የምትለው ወጣት ይዲዲያ፤ ጌጣጌጦቹ ከጥይት ቀለሃ የሚሠሩ ሲሆን፣ ሙሉ ለሙሉ በእጅ የሚሠሩ ናቸው፤ ለመሥራት ምንም አይነት ማሽን እንደማይጠቀሙም ትናገራለች። ጌጣጌጦች ለማምረት (አንድ የእጅ ወይም የአንገት ጌጥን) ለመሥራት የሚወስደው ጊዜ እንደሚሠራው ሥራና ዲዛይን አይነት የሚለያይ መሆኑን ጠቅሳ፤ ከግማሽ ቀን እስከ ሦስት ቀናት ጊዜ የሚፈጁ የጌጣጌጥ ሥራዎች መኖራቸው ተናግራለች።

ወጣቷ፤ ጌጣጌጦቹ በአብዛኛውን ሴቶች የሚጠቀሟቸው ቢሆኑም፤ ለወንዶችም እጅ ላይ የሚጠለቅ ጌጦችን እንደሚሠሩ ትናገራለች። ወጣት ይዲዲያ እንደምትለው፤ ጌጣ ጌጦቹ ሁሉንም የሚያማክሉና ባሕላዊ ይዘት ያላቸው መሆናቸው በሁሉም የእድሜ ክልል ላይ የሚገኙ ሴቶች ያጌጡበታል። በተለይ ከባህላዊ አልባሳት ጋር አብረው የሚሄዱ ስለሆኑ በሁሉም ተመራጭ ያደርገቸዋል። ዋጋቸውም የኅብረተሰቡን የመግዛት አቅም ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ጌጣጌጦች የሚሠሩበት ቁሳቁስ፣ የጥሬ እቃው አቅርቦት፣ የሚፈጀው ጊዜና ጉልበት ተለክቶ ዋጋ የሚሰላ ሲሆን በየጊዜው ዋጋ ልዩነት አለው።

አሁን ላይ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ዜጎች ደንበኞች እንዳላቸው የምትናገረው ወጣት ይዲዲያ፤ ምርቶቹን ከሀገር ውስጥ ገበያ ባለፈ ለውጭ ሀገር ገበያ የሚያቀርቡበት ዕድል ስለመኖሩ ትናገራለች። በከተማው ባሉት ሦስት ሱቆች ምርቶቻቸውን ለሽያጭ እንደሚያቀርቡም ጠቅሳ፤ ከሀገር ውጭ በአሜሪካ፣ በካናዳና በሌሎች ሀገራትም እንዲሁ በመላክ ለገበያ እንደሚያቀርቡ ገልጻለች። ከዚህ በተጨማሪ የጌጣጌጥ ምርቶች ለማስተዋወቅ የተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ፣ ቴሌግራም፣ ኢንስታግራም እና የመሳሰሉ) አማራጮችን በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እንደሚያደርጉ ትገልጻለች።

«እስካሁን ጌጣጌጦችን የሚገዙ ደንበኞቻችን ስለጌጣጌጦቹ አሠራር የሚሰጡን አስተያየት በእጅጉ የሚያበረታቱ ተጨማሪ ሥራዎች እንድንሠራ የሚያደርጉ ናቸው» የምትለው ወጣት ይዲዲያ፤ አሁን የምንሠራቸው ዲዛይኖች የበለጠ እንድናሻሽልና በዘመናዊ መንገድ እንድናቀርብ የሚያስችሉ ናቸው ብላለች። አሁን ላይ ደንበኞች ተሠርቶ የቀረበውን አይነት ከመውሰድ ይልቅ የሚፈልጉትን የጌጣጌጥ አይነት በመግለጽ በሚፈልጉት ቅርጽና ዲዛይን በምርጫቸው መሠረት በትዕዛዝ እንደሚያሠሩም ገልጻለች።

የጌጣጌጥ ሥራን የምትሠራው ወጣት ሰላማዊት በቀለ በበኩሏ ወደ ጌጣጌጥ ሥራ የገባችው በኮቪድ ወቅት እንደነበር ገልጻ፤ ከተለያዩ ነገሮች የጆሮ ጌጥ ለመሥራት ያደረገችው ሙከራና ከሠራችላቸው የቅርብ ዘመዶቿ ያገኘችው ምላሽ ውስጣዊ ፍላጎት እንዲያድርባት እንዳደረጋትና በዚያው በሥራው ተመስጣ መቅረቷን አጫውታናለች።

ሰላማዊት፤ ጌጣጌጦችን ከጨሌ፣ ከክር፣ ከብረታ ብረት፣ ከዶቃ እና ከተለያዩ ነገሮች የምትሠራ ሲሆን፤ ጌጦቹን በተለያዩ ቅርጽና ዲዛይን እያሳመረች ሙሉ በሙሉ በእጇ እንደምትሠራቸውና የእጅ ሥራዎች እንደሆኑ ትናገራለች።

የምትሠራቸው ጌጣጌጦች የጆሮ፣ የአንገት፣ የእጅ እና የእግር ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም በበዓላት ጊዜ (ለአሸንዳ፣ ለመስቀል፣ ለእሬቻና ለመሳሰሉት) የሚፈለጉና የሚደረጉ ጌጣጌጦችን እንደምትሠራ ትናግራለች፡፡

እነዚህን የጌጣጌጥ ምርቶች የምትሸጥበት መሸጫ ቦታዎች ባይኖሯትም በተለያዩ ወቅት በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ላይ በማቅረብ እንደምታስተዋውቅና የማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ተደራሽ እያደረገች መሆኑን ትናገራለች።

ጌጣጌጦቹ በእጅ የሚሠሩ እንደመሆናቸው ጊዜና ጉልበት የሚጠይቁ ናቸው የምትለው ወጣት ሰላማዊት፤ ሆኖም ግን ለሥራው ካላት ከፍተኛ ፍላጎት የተነሳ ሥራውን በፍጥነት እንድትሠራ የሚያደርጋት መሆኑን ተናግራለች። ጌጣጌጦቹን ሁሉም ሰው በሚችለው አቅም ገዝቶ የሚጠቀምባቸው ተመጣጣኝ ዋጋ ያላቸው ሲሆን፤ ዋጋቸውም 100 እስከ 350 ብር ድረስ የሚሸጡ እንደሆኑ ገልጻ፤ ብዙዎች ያለችበት ቦታ ድረስ ፈልገው በመምጣት እንደሚገዟት ነው ያጫወተችን። በቀጣይም ጌጣጌጦችን ከተለያዩ ነገሮችና በተለያዩ ቅርጽና ዲዛይኖች በመሥራት ተደራሽነቷን የማስፋት እቅድ እንዳላት ነው የገለጸችው።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ስድብ የጀግንነት ወይስ የፍርሃት?

**ዋስልኝ አየለ**

አንድ የሥራ ባልደረባዬ የነገረኝ የራሱ ገጠመኝ ነው። ጠዋት በታክሲ ወደ ሥራ ቦታ እየሄደ ነው። ለትራንስፖርት ከከፈለው ውስጥ የ5 ብር መልስ አለው። ቢጠብቅ ቢጠብቅ መልስ ረዳቱ አልሰጠውም። መውረጃው ሲደርስ ከታክሲው እየወረደ «መልስ ስጠኝ» አለው። ረዳቱም «ይሄውልህ አህያ!» ብሎ አምስት ብሩን ሰጠው። ይሄኔ እሳት ለብሶ እሳት ጎርሶ ረዳቱን አነቀው። ሌሎች ተሳፋሪዎች መካከረውና ገላግለዋቸው ነገሩ በዚሁ አለቀ።

እግዲህ አስቡት! «መልስ ስጠኝ» ከማለት ውጭ ምንም የተነጋገሩት መጥፎ ነገር የለም። ከዚያ በፊትም አይተዋወቁም፤ ያገናኛቸው ይሄ ሥራ ብቻ ነው። በዚያች ቅጽበት፣ በአንዲት ቃል ነው ረዳቱ አፉ እንደለመደ ያንን ነውር ስድብ የተሳደበው።

«እንዴት ከታክሲ ረዳት ጋር ትጣላለህ?» ስለው «እኔም በኋላ ያናደደኝ ከታክሲ ረዳት ጋር መሆኑ ነው» አለኝ። ለመጣላትም አቻ ሳያስፈልግ አይቀርም፤ እነዚህ ልጆች (የታክሲ ረዳቶች) ስድብን መደበኛ ሥራቸው አድርገውታል። ሁሉም ናቸው ለማለት ባያስችል እንኳን በጣም ሲበዛ ባለጌዎች ናቸው። ለመሳደብ በማያደርስ ሁኔታ ዝም ብለው ከስድብ ይጀምራሉ። ትልልቅ ሰዎች ደግሞ ክብራቸው ሲነካ አይወዱም። ክብሩን ጠብቆ፣ በጨዋነትና በትህትና የሚስተናገድ ሰው ማንም ዝም ብሎ ስድ ባደገ አፍ ሲሰድቡት መናደዱ አይቀርም።

የታክሲውን መነሻ ያደረኩት በቅርብ ከሰማሁት ገጠመኝ ልነሳ ብየ እንጂ ስድብ በታክሲ ረዳቶችና ሾፌሮች የተገደበ አይደለም። እንዲያውም የጠቅላላ ሾፌሮች መገለጫ እስከሚመስል ድረስ አንገታቸውን አሾልከው ሲሰዳደቡ ነው የምናየው። «ከመንጃ ፈቃድ ጋር ስድብ አብሮ ነው እንዴ የሚሰጣቸው!» እየተባለ ሁሉ ይቀለዳል።

እንደ አጠቃላይ መሳደብ የኋላቀርነት፣ የሞራለቢስነት እና የፈሪነት ምልክት ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ የሚያናድድ ነገር ሲፈጠር ሊያጋጥም ይችላል እንበል። ዳሩ ግን ምንም በሌለበት፣ በጨዋነት እየተስተናገደ ያለውን የሠለጠነ ሰው ብድግ ብለው የሚሳደቡ አሉ። ሰው አንዳንድ ጊዜ በሁኔታዎች ስሜታዊ ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን ከሳቅና ፈገግታ ሁነት ላይ ተነስተው አንድን ነገር ለመጠየቅ በስድብ የሚጀምሩ አሉ። ይሄ ለሚሰደበው ሰው ምን ያህል እንደሚያናድድ አይገባቸውም።

ልክ ነው ልክ አይደለም የሚለውን እንተወውና አንዳንድ ጊዜ በጓደኝነት (በትውውቅ) የፍቅር መሰዳደቢያዎች አሉ። ይህን አውቃለሁ። ይህ የሚሆነው ግን ለሚተዋወቁና ለሚግባቡ ሰዎች ብቻ ነው። የምሩን ተኮሳትሮና ተናዶ፤ የማያውቀውን ሰው የሚሳደብ ግን ኋላቀር የሆነ ሰው ብቻ ነው።

በወጣቶች ዘንድ፣ በልጆች ዘንድ፣ እንዲሁም በታክሲ ረዳቶች ዘንድ ብቻ የተገደበ ቢሆን አይደንቀኝም ነበር፤ ጉዳይ ሊሆንም አይችልም ነበር። ዳሩ ግን እንደ ማኅበረሰብ ምን ያህል ብዙ እንደሚቀረን የሚያሳየን እና ጉዳዩን አሳሳቢ የሚያደርገው፤ የሞራል እና የሥልጣኔ ምሳሌ መሆን በሚገባቸው የተማሩ ሰዎች ላይ በስፋት የሚስተዋል መሆኑ ነው። ውድ መኪና ይዘው፣ ውድ ልብሶችን ለብሰው፣ ትልቅ ቦታ ላይ ያሉ ሆነው፣ በእግረኛ መንገድ ላይ እየሄደ ያለ ሰው የሚሳደቡ አሉ። በተቋማት ውስጥ ለተለያየ ጉዳይ የመጣ ሰው ትንሽ ነገር ሲሳሳት ከማስረዳት ይልቅ የሚሳደቡ አሉ። እነዚህ ሁሉ ለምን ሆኑ ከተባለ መሠልጠን ገና ብዙ ስለሚቀረን ነው።

በተደጋጋሚ እንደምለው የሠለጠኑ ናቸው የሚባሉ ሀገራት ሠለጠኑ የተባለው በቴክኖሎጂ እና በመሠረተ ልማት ባላቸው ምጥቀት ብቻ አይደለም። የሠለጠኑ ናቸው የተባሉት አዕምሯቸው የሠለጠነ ስለሆነ ነው። የሞራል ከፍታ ስላላቸው ነው። ሰው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ስለሚከበሩ ነው። ነውር የሆኑ ነገሮችን ስለማያደርጉ ነው፡፡

ምንም እንኳን የሞራል እና በጎ እሴቶች ባለቤት ብንሆንም በዚያው ልክ ግን ብዙ ነውር የሆኑ ነገሮችን እናደርጋለን። ከመሬት ተነስቶ የአንድን ሰው ክብር መንካት ነውር ብቻ ሳይሆን ወንጀልም ጭምር ነው። ብዙ የክብር መገለጫ የሆኑ እሴቶች እንዳሉን ሁሉ፣ ብዙ ክብረ ነክ የሆኑ ድርጊቶችና ንግግሮችም አሉን። አሳዛኙ ነገር ግን እነዚህ ነውር ነገሮች የተማሩ በሚባሉ እና የመሠልጠን አርዓያ ሊሆኑ በሚገባቸው ሰዎች የሚባሉ መሆናቸው ነው፡፡

### ስመሆኑ ግን ስድብ የጀግንነት መግለጫ ነው ወይስ የፍርሃት?

ስድብን ባሕል ያደረግነው ሁሉ ይመስላል። ምክንያቱም ተሳዳቢ ሰዎችን እንደ ደፋርና ጀግና የሚቆጥሩም አሉ። ተሰዳቢውን እንደ ተዋረደ አድርገው ሰዳቢውን እንደ ደፋር የሚቆጥሩ ሰዎች አሉ። የተዋረደው ግን ሰዳቢው ነው። መሳደብ ጀግንነት ሳይሆን ፍርሃት ነው። ማስተዋል የማይችሉ ሰዎች መገለጫ ነው። የሆነ ነገር ይመጣብኛል ብሎ የሚፈራ ሰው ነው የሚሳደብ።

መሳደብ በራስ ያለመተማመን ምልክት ነው። አንድ ሰው ትሑትና ትዕግስተኛ የሚሆነው በራሱ ሲተማመን ነው። በአንፃሩ ግልፍተኛና ወፈፌ የሚሆነው ደግሞ ተጠራጣሪ ሲሆን ነው። በትንሽ ነገር የበታችነት ስሜት ስለሚሰማው ነው። የሚሳደቡ ሰዎች ምናልባትም በውስጣቸው የሚረበሹበት ነገር ስላለ ነው። በውስጣቸው ቁስል ሲኖር ነው።

በአንፃሩ ትዕግስተኛ፣ አስተዋይና በሀሳብ የሚያምኑ ሰዎች ደግሞ በራሳቸው የሚተማመኑ ሲሆኑ ነው። ስቀው ሊያልፉት ሁሉ ይችላሉ። ስቆ ለማለፍ ደግሞ በጣም የተረጋጋ አሳቢነት ይጠይቃል። ያ የተሰደበበት ነገር እንደማይወክለው፣ ተሳዳቢው በራሱ ችግር የተሳደበ መሆኑን ያውቃል ማለት ነው። እንዲያውም ለተሳዳቢው ሰውየ ስብዕና ሊያዝን ይችላል። «ምን ሆኖ ይሆን?» በሚል ለሕይወቱ ሊያዝንለት ይችላል። ምክንያቱም ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ የሚሳደብ ሰው የሆነ ችግር አለበት ማለት ነው፡፡

በእንዲህ አይነት ማኅበረሰብ ውስጥ የሚያሳዝኑኝ ቀድመው የነቁና የሠለጠኑ ሰዎች ናቸው። የራሳቸውንም የሌላውንም ክብር ጠብቀው እየተንቀሳቀሱ ሳለ በአንዳንድ ባለጌዎች ግን ሊሰደቡ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት የማያምኑበትን መደባደብም ሊገቡበት ይችላሉ ማለት ነው። በሥነ ሥርዓት የተቀመጠውን ሰው በስድብ «ወዲህ ጠጋ በል፣ ወዲያ ዞር በል....» የሚል ይኖራል። በተለይም ሕጋዊ ያልሆነ አሠራርን የሚከተሉ ሰዎች «ለምን?» ተብለን እንጠየቃለን ብለው ስለሚፈሩ በቁጣ እና በስድብ ይጀምራሉ።

በአንዳንድ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች የምታዘበው ነገር ደግሞ፤ አንዳንድ ባለጉዳይ ሆን ብሎም ይሁን ባለማወቅ አሠራሩ ከሚፈቅደው ውጭ አገልግሎት ለማግኘት ይጠይቅ ይሆናል። በዚህን ጊዜ አገልግሎት ማግኘት እንደማይችል በትሕትና መንገር ሲቻል በቁጣ እና በስድብ የሚናገሩ አሉ። ለምሳሌ ሰዓት አሳልፎ የመጣ ሰው፤ ሰዓቱ እንዳለፈና እንደማይቻል መንገር ሲቻል «የታባክ ቆይተህ ነው» በሚል ስድብ እና ቁጣ ያመናጭቁታል። መከልከልንም እኮ በትሕትና መንገር ይቻላል፡፡

ይሄ ነገር ልማድ ከመሆኑ የተነሳ ባለጉዳዩም በትሕትና ካናገሩት ፊት የሰጡት ይመስለውና ከሕግና አሠራሩ ውጭ አገልግሎት ማግኘት ይጓጓል። እንደማይቻል በትሕትና ከነገሩት ለልመና ምቹ የሆኑ ይመስለዋል። ስለዚህ ቁርጡን እንዲያውቅ በቁጣ ይከለክሉታል ማለት ነው። ስለዚህ የሁሉም ችግር ነው፡፡

ስድብ የኋላቀርነት መገለጫ ነው! መሠልጠንን አለባበስ ላይ ብቻ አናድርገው! የሞራል እሴቶቻችንን እንጠቀም!

# ዓለም አቀፍ

## ሩሲያ የአውሮፓ ህብረትን አስጠነቀቀች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሩሲያ የአውሮፓ ህብረትን አስጠነቀቀች። ለአንድ ሳምንት ልዩ ዘመቻ በሚል የተጀመረው የሩሲያ-ዩክሬን ጦርነት 20ኛ ወሩ ላይ የሚገኝ ሲሆን ጦርነቱ በርካታ ትዕይንቶች ተስተናግደውበታል፡፡

የአውሮፓ ህብረት በሩሲያ ላይ በርካታ ማዕቀቦችን የጣለ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሩሲያ መንግሥት እና ዜጎች ንብረት የሆኑ የባንክ መዝገቦችን እንዳይንቀሳቀሱ አግዷል። በአጠቃላይ በህብረቱ እገዳ የተጣለበት የሩሲያውያን ገንዘብ 223 ቢሊዮን ዶላር ሲሆን ይህ ገንዘብ ለዩክሬን መልሶ ግንባታ እንዲውል መወሰኑ ተገልጿል፡፡

የህብረቱ ፕሬዚዳንት ኡርሱላ ቮን ደር ሊን ዩክሬን ለደረሰባት ውድመት ካሳ አልያም ለመልሶ ግንባታ በሩሲያ ወጪ መሸፈን አለበት ሲሉ ተናግረዋል። ሩሲያ ለህብረቱ በሰጠችው ምላሽ የአውሮፓ ህብረት የሩሲያውያንን ገንዘብ ለዩክሬን ከሰጠ የአጸፋ ርምጃ እንደምትወስድ አስታውቃለች፡፡

የአውሮፓ ህብረት ሀገራት በሩሲያ ምን ያህል ገንዘብ እንዳላቸው በግልጽ ያልተጠቀሰ ሲሆን ህብረቱ ያሰበውን ሕገወጥ ሥራ እንዲያቆም ሞስኮ አሳስባለች፡፡

ከ22 ቀናት በፊት በእስራኤል እና ሃማስ መካከል የተፈጠረው ጦርነት አሜሪካ እና የአውሮፓ ህብረት ትኩረታቸውን ከዩክሬን ላይ እንዲያነሱ ማድረጉ እየተገለጸ ይገኛል። ይህን ተከትሎም ሩሲያ በዩክሬን ላይ እያደረገች ያለውን የአየር እና የምድር ላይ ጥቃት አስፋፍታለች



**የአውሮፓ ህብረት 223 ቢሊዮን ዶላር የሩሲያን ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ አግዷል**

የተባለ ሲሆን ዩክሬን በበኩሏ የጦር መሣሪያ ድጋፍ እንዲደረግላት በመጠየቅ ላይ ትገኛለች፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በዩክሬን በቀጣዩ መጋቢት ወር ላይ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ይደረጋል መባሉ ዩክሬናውያንን እና አጋሮቿን የከፋፈለ ሲሆን ፕሬዚዳንት ዘለንስኪ በምርጫው ሊሸነፉ ይችላሉ የሚል ስጋትም



## አሜሪካ የጦር መሣሪያ ንግድን አገደች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የዓለማችን ልዕለ ሃያሏ ሀገር አሜሪካ የጦር መሣሪያ ንግድ እንዳይካሄድ ማገዷን የሀገሪቱ ንግድ ሚኒስቴር አስታውቋል። ከአሜሪካ የጦር መሣሪያ ፋብሪካዎች ለሀገር ውስጥ እና ሌሎች ሀገራት የጦር መሣሪያዎችን በመላክ ንግድ የተሰማሩ ግለሰቦች እና ተቋማት በውሳኔው ማዘናቸውን አስታውቀዋል፡፡

የሀገሪቱ ንግድ ሚኒስቴር የጦር መሣሪያ ለጊዜው መታገዱን ከመናገሩ ውጪ ለምን እንዳገደ ግልጽ አለማድረጉን ሮይተርስ ዘግቧል። የጦር መሣሪያ ንግዱ ወታደራዊ ተቋማትን ወይም መንግሥታዊ አካላትን አይመለከትም የተባለ ሲሆን የጦር መሣሪያ ንግድን ለ90 ቀናት እንደታገደ ተገልጿል፡፡

እገዳው የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ እና ብሔራዊ ደህንነትን የማስጠበቅ አካል ነው የተባለ ሲሆን እንደ ዩክሬን፣ እስራኤል እና ሌሎች ቁልፍ ወዳጅ ሀገራትን እንደማይመለከት ተገልጿል፡፡

ለንግድ ዓላማ እንዳይውሉ ከታገዱ የጦር መሣሪያዎች መካከል የእጅ የጦር መሣሪያን እና መነጽሮችን ይመለከታል የተባለ ሲሆን በቀጣዮቹ ሶስት ወራት ውስጥ እገዳው ያመጣው ለውጥ ከተገመገመ በኋላ ሊነሳ እንደሚችል ተገልጿል፡፡

የጦር መሣሪያዎችን ወደ ውጭ ሀገራት በመላክ ይተዳደሩ የነበሩ ፋብሪካዎች እና ነጋዴዎች በእገዳው ይጎዳሉ የተባለ ሲሆን አዲስ የጦር መሳሪያ ንግድ ማውጣትም አብሮ ታግዷል ተብሏል፡፡

ይሁንና ለመንግሥት ተቋማት የጦር መሣሪያ የሚሸጡ ነነጋዴዎች ሥራቸውን መቀጠል ይችላሉ የተባለ ሲሆን ተቀባይ ሀገራትን በግልጽ ማስቀመጥ እና ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ እገዳው እንደማይመለከታቸው ተገልጿል፡፡


**በጉምሩክ ኮሚሽን አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተያዙና የተወረሱ የተሽከርካሪና ልዩ ልዩ ዕቃዎች ሽያጭ ጨረታ ማስታወቂያ የጨረታ ቁጥር 17/2016**

አዲስ አበባ ቃሊት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የተተው፣ የተወረሱ እና በኮንትሮባንድ ተይዘው የሚገኙ የተለያዩ የቤትና የጭነት ተሽከርካሪዎች (DUMP TRUCK፣ IVECO FIAT፣ TOYOTA HAILUX፣ TOYOTA COROLLA፣ TOYOTA VITZ፣ TOYOTA HAICE፣ TOYOTA YARIS፣ TOYOTA CHR፣ HYUNDAI፣ SUZUKI፣ MISTUBUSHI)፣ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎችን፣ የሞባይል ክፍሎች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን፣ የተለያዩ የተዘጋጁ አልባሳትና ጫማዎች፣ የውብት መጠበቂያ ዕቃዎች እና ሌሎች የተለያዩ ዕቃዎችን ባሉበት ሁኔታ በግልፅና በሃራጅ ጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል። ከዚህ በታች በቅፁ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ለጨረታ የሚቀርቡ ንብረቶች ዝርዝር መረጃ ተዘጋጅቶ ከሀሙስ ጥቅምት 22 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ለተጫራቾች በሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ላይ የሚታወቅ መሆኑ እንገልጻለን። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች የጨረታ ሰነድ ከቀን 20/02/2016 ዓ.ም ጀምሮ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሆኑም፡-**

1. በቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በጨረታ በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር የሚፈልግ ማንኛውም በዘርፉ የፀና የንግድ ፍቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ፣የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፍኬት እና የዘመኑን ግብር የከፈለ ስለመሆኑ ከግብር ሰብሳቢ መሥሪያ ቤት የተሰጠ ማስረጃ ሰነዶች ኮፒ እና የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኢንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን ለሃራጅ ጨረታ ደግሞ ከጨረታ አንድ ቀን በፊት ይዞ ማስመዝገብ ይኖርበታል፡፡
2. የሚሸጠው ዕቃ ተሽከርካሪ ከሆነ ማንኛውም ዕድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በተ.ቁ 1 የተገለፁ ቅድም ሁኔታዎቹን ማሟላት ሳያስፈልገው የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ ወይም (C.P.O) ከመጫረቻ ሰነዱ ጋር አያይዞ በኢንቨሎፕ ወይም በፖስታ በማሸግ ለጨረታ በተዘጋጀዉ ሳጥን ውስጥ በማስገባት በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች የግልፅና የሀራጅ ጨረታውን ሠነድ ዘወትር በስራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ) በመክፈል በቅ/ጽ/ቤቱ በመገኘት የጨረታ ሠነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
4. በግልፅ ጨረታ ለመሳተፍ ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች የሰጡትን ዋጋ አምስት በመቶ (5%) ለጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) በቅ/ፅ/ቤቱ አድራሻ ስም CUSTOMS COMMISSION ADDIS ABABA KALITY CUSTOMS BRANCH OFFICE አዲስ አበባ በሚገኙ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አሰርተው ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ለተሽከርካሪ ሐራጅ ጨረታ እና የዕቃ ሐራጅ ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ እና ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች ብር 100,000.00 የጨረታ ማስከበሪያ ቼክ (CPO) ተጫራቹ ማስያዝ አለበት፡፡
6. ተጫራቾች በሚከተለው የጨረታ ቀናት (ስኬጁል) መሰረት መጫረት ይችላሉ፡፡

| ተ.ቁ | የቅ/ጽ/ቤቱ ስም | የጨረታው ዓይነት | የንብረት መመልከቻ ቀን የጨረታ ሰነድ ከወሰዱ ቀን ጀምሮ | የጨረታው የመዝጊያ እና የመክፈቻ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አ.አ ቃሊቲ ሃራጅ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት | ሃራጅ | እስከ 26/02/2016 | ጥቅምት 27/02/2016 4:00 ሠዓት ጀምሮ ይካሄዳል፡፡ |
| | | ግልፅ | እስከ 27/02/2016 | ጥቅምት 28/02/2016 3:45 ተዘግቶ በዚያውኑ ቀን 4:00 ሠዓት ይከፈታል፡፡ |

7. **የጨረታው መክፈቻ ቦታ፡-**አ.አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የሚካሄድ ሲሆን ጨረታው ተጫራቾች /ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባሉበት ወይም በታዛቢዎች ፊት ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች ለጨረታው ዋስትና ያስያዙት (CPO) ከሚከፍሉት ዋጋ ጋር የሚታሰብላቸው ሲሆን ለተሸናፊ ተጫራቾች ደግሞ የጨረታው ውጤት ከተገለፀ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ተመላሽ ይደረግላቸዋል ፡፡
9. አሸናፊ ተጫራቾች ማሸነፋቸውን ከተገለፀላቸው ቀን ጀምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ያሸነፉበትን ገንዘብ ገቢ በማድረግ ዕቃውን ማንሣት ይኖርባቸዋል፡፡
10. ከላይ በተ/ቁ 9 በተገለፁት ቀናት ውስጥ ክፍያውን ገቢ ያላደረጉ እና ንብረቱን ተረክቦ ያልወሰዱ ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበርያ ያስያዙት እና ለንብረቱ የከፈሉት ዋጋ ለመ/ቤቱ ገቢ ሆኖ ዕቃው በድጋሚ ለሽያጭ ይቀርባል፡፡
11. መ/ቤቱ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ በስልክ ቁጥር፡-**አዲስ አበባ ቃሊት ጉምሩክ 011 - 470 - 85- 03

**በጉምሩክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ቃሊት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት**

# ነፃ ሃሳብ

# በመመካከር ለሀገራችን ሰላም፤ ለሕዝባችንም አንድነትን እናጽና

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገራችን ኢትዮጵያ በተግባቦት መንፈስ ሀገራዊ አንድነትን ለመፍጠር የምክክር ኮሚሽን አቋቁማ፤ ከዛም አለፍ ሲል የተለያዩ የምክረ ሀሳብ መድረኮችን አዘጋጅታ የአንድነት ጎዳናዎቿን በማሰናዳት ላይ ትገኛለች። ከሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አንጻር ስንቃኘው ያለፉትን ሁለትና ሦስት ዓመታት ሀሳብ በማሰባሰብና ምቹ የአንድነት ጎዳናዎችን በመጥረግ ሂደት ላይ ተጠምዶ ቆይቷል። አሁን ላይ ደግሞ ቅድመ ዝግጅቱን አጠናቆ ለውይይት የሚያበቃውን የመጨረሻ ምዕራፍ ተግባር ላይ እንደሚገኝ ነው መረጃዎች የሚጠቁሙት።

ከዚህ አኳያ ሲታይ አሁን እንደ ሀገር ከምንግዜውም በላይ ራሳችንን ለተግባቦት የምናዘጋጅበት ጊዜ ላይ ነን። ምክንያቱም ባለመግባባትና ያለፈን በማስታወስ የከፈልናቸው ዋጋዎች ዛሬም ጥዝጣዜአቸው አልሻረም። የባለፈው ጊዜ ጦርነት፣ የባለፈው ጊዜ የብኩርና ሽሚያ ዛሬ ላይ ብዙ ዋጋዎችን እየከፈልን እንደሆነ እኔና እናንተ ምስክሮች ነን።

በመሆኑም ይሄንን ችግር መሻገር የሚያስችለንን ምክክር ካላደረግን፤ እንዲሁም ከልብ በሆነ ስሜት ለይቅርታና እርቅ ራሳችንን ካላዘጋጀን በዚሁ አግባብ ችግሩን ካልተሻገርን፤ የሚመጣው ካለፈው የሚብስ ነው የሚሆነው። ያለፉት የእውነትም ሆኑ የሐሰት ትርክቶችን ዘግተን በአዲስ መነቃቃት መጪውን ስንቀበል ነው የጥንቱ ኃያልነታችን የሚመለሰው።

እኛን እና ታሪካችንን በተመለከተ ሁልጊዜም አንድ እውነት አለ። ፍቅርን የቋጠረ፣ አንድነትን ያቀለመ አብሮነት መነሻችን እና መድረሻችን ነው። ዓለም ያወቀንና የተቀበለን በዚህ ማንነታችን በኩል ነው። በዚህ ረገድም የገባን ብዙ ቢሆንም፤ እንደገባን አለመኖራችን ግን እየጎዳን ነው። በትላንት ጉያ ውስጥ ያሉ የጀግንነትና የሉዓላዊነት፣ የነፃነትና የዘመናዊነት ቀንዲሎቻችን፣ የአብሮነት ውጤቶቻችን እንደሆኑ እያወቅን እንኳን ለዚህ ክብር ዋጋ ስንከፍል አንታይም።

ኢትዮጵያ ለፍቅር ማደያ ናት። እኛ ለሰላምና ለአብሮነት መነሻ ታሪኮች ነን። አሁን ላይ ብርቅ የሆኑብን ዘመናዊነትና ሥልጣኔዎች፣ ፈተኝነትና ቀዳማዊነት ከእኛ ተነስተው ወደ ዓለም የተሰደዱ ናቸው። ታዲያ ለምን ራቁን? ለምንስ ሸሹን? ከተባለ፤ መልሴ፣ ከፍቅር ስለራቅን ነው የራቁን፤ ከአንድነትና ከአብሮነት ስለሸሸን ነው የሸሹን የሚል ሆናል።

በመሆኑም ወደዚህ የፍቅር ሰገነታችን፤ የአንድነት መድረካችን ለመመለስ ሰፊ የመነጋገሪያ ሜዳ ያስፈልገናል። ዘረኝነትና ብሔርተኝነት ደብዝዘው ኢትዮጵያዊነት ብቻ የሚቀነቀንበት ፖለቲካ፣ ራስወዳድነትና ጥቅመኝነት ኮስሰው አብሮነት የሚጎመራበት መድረክ ያሻናል። ምክንያቱም አዕምሯችንን አጽድተን ልዩነቶቻችንን እስካላጠበብን ድረስ ችግሩ ከመባስ ባለፈ የሚሻል ሕመም አይኖረንም። ሳይቃጠል በቅጠል.. የሚለው አባባል እዚህ ጋ መነሳቱ ግድ ነው። የባሰ ዋጋ ሳንከፍል፣ ከዝቅታ ወደ መደፋት፣ ከድጡ ወደማጡ ሳንገባ አብሮነታችንን የምንመልስበትን እድል መፍጠር ይጠበቅብናል ።

ከየትኛውም በጎ ነገር በላይ እድሎቻችን በመነጋገር ውስጥ ነው ያሉት። የሰው ልጅ ወደዚች ምድር ሲመጣ በፍላጎት፣ በምኞት እንዲሁም በተለያየ ሀሳብ ተከሽኖ ነው። አይደለም ከሌላው ጋር ከራሳችን ጋር እንኳን የማንግባባበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ ተነጋግረን እንድንግባባ፣ ተመካክረን አብረን እንድንኖር ልዕለ አዕምሮ ተሰጥቶናል።

አእምሮ ልዩነቶችን ለማስታረቅ ትልቁ አቅም ነው። የይቅርታና የፍቅር ዋጋን ለማሰላሰል ጥልቁ ጉልበት ነው። ጥላቻን በፍቅር ለመቀየር፣ በእርቅና በምክክር ወደአብሮነት ለመመለስ ነው ኃይል ነው። ለጥላቻ እየበረታ ለፍቅር የሚደክም አዕምሮ አልተሰጠንም። እንዲያውም ሚዛን ላይ እናውጣው ካልን የተሰጠን አዕምሮና ልብ ከፍቅር ውጪ ጥላቻን የማያውቅ ነው። ታላቁ የነፃነት አባት ኔልሰን ማዴላ ይሄን እውነት ሲገልጸው ‹ፍቅር ተፈጥሯዊ፣ ጥላቻ ግን በትምህርት የምናገኘው ነው› ብሎ ነው።

ከዚህ የነፃነት ታጋይ አስተምህሮም ሆነ ከሌላ ዓለማዊና መንፈሳዊ ንጻሬ አኳያ ስናየው በመካከላችን ያለው የእኔ የእኔ ሽኩቻ እንደፖለቲካ ባሉና ራስን ብቻ ከመጥቀም አባዜ ከሚመነጩ፣ ርህራሄ አልባ እሳቤዎች የተፈጠሩ እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ያለፉትን በርካታ ዓመታት አዕምሯችን ለአንድነት የሚሆን ዋጋ ሲከፍል አልታየም። በጥሎ ማለፍ ውስጥ የጎለመሰ ነው። የጥሎ ማለፍ እሳቤ ደግሞ ትውልዱን መሰል ኢ-ሰብዓዊ ልምምዶችን እያስተማረ ሀገርን ባዶ የሚያስቀር ነው።

ፖለቲካችን አሁን ላሉብን ማኅበራዊ ነውጦች ጣት የሚቀሰርበት የመጀመሪያው ተጠያቂ ነው። ይሄ የብዙዎቻችን እምነት ቢሆንም ፖለቲካውን ለማጥራት ጥረት ስናደርግ ግን አንታይም። የሚመጣውም ሆነ የሚሄደው ፖለቲከኛ ሥልጣንን ለሕዝብ ሰጥቶ ሀገርን በማገልገል መንፈስ ውስጥ መጥቶ የሄደ ፖለቲከኛ የለም። ይሄን አይነቱ ራስን ማዕከል ያደረገ ልምምድ ትውልዱን ለራስ ወዳድነትና ለጥቅመኝነት ዳርጎታል።

ሀገር የፖለቲካ መልክ ናት። እኔና እናንተ ሳንቀር እንኳን ከማኅበረሰባችን በላይ ፖለቲካ ጸንሶ የወለደን የፖለቲከኞቻችን የአስተሳሰብ ውጤቶች ነን። እዛ መንደር መነጋገርና መግባባት ቢኖር እኔና እናንተ መንደር ተነጋግሮ መግባባት አይቸግረንም። ፖለቲከኞቻችን ያሸረጡትን የራስወዳድነት ሸርጥ አውልቀው አንድነትን ይልበሱ። ያኔ ሕዝብ ማቁን አውልቆ ፀዓዳውን ይለብሳል። ዓላማችን በእርቅና በተግባቦት ኢትዮጵያን ማስቀጠል ከሆነ፣ ለጥላቻ የበረታ አዕምሯችን ለፍቅር እንዲንበረከክ እናለማምደው። ሕዝብ ተኮር በሆነ ብዙኃነት በፖለቲካችን አናት ላይ የፍቅር ፀሐይ ትውጣ።

ይቺ ሀገር የእኔና የእናንተ አንድነት ካላጸናት፣ የውጪ ርዳታና ድጎማ አያጸናትም። ሁሉም በክፍተቶቻችን እየገቡ መፍትሔ አልባ መለያየትን የሚፈጥሩብን ናቸው። በነጠረና ብዙኃነትን በተላበሰ ምክረ ሀሳብ ቀዳዳዎቻችንን ደፍነን መጪውን ጊዜ እስካልተቀበልን ከዝቅታ የሚታደገን አይኖርም። በጀመርነው የምክክር መድረክ ላይ ሀሳብ በመስጠትና በመቀበል ኢትዮጵያን ማሻገር ለነገ የማንለው ኃላፊነታችን ነው።

ታላላቅ ሥልጣኔዎች ከሃሳብ የሚጀምሩ ናቸው። ዘመን ተሻጋሪ በሆነ የብዙኃነት እውነት ምድርን ያቆነጁ ተግባራት እንኳን መነሻቸው ሀሳብ ነበር። የነሶቅራጠስና የነአርስቶትል ተራማጅ አመለካከት ዛሬም ድረስ ሕይወታችን ሆኖ በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የሚኖረው ምክንያታዊነትን ባዘለ መንገድ ነው። ሀሳቦቻችን ምክንያታዊነትን ያዘሉ ከሆኑ ወደ ከፍታ የማይሄድበት ምንም ምክንያት የለም። ሀሳቦቻችን ለአንድነት መንገድ በሚዘጋ ራስወዳድነት ውስጥ ከሆኑ ግን በምንም መፍትሔ አናገኝም።

አጉል መሻት ከሸነቆረው የዘረኝነትም ይሁን የጥላቻ ቀዳዳ መውጫችን ምክረ ሀሳብ ነው። በሀሳብ ካልተሸናነፍን በምንም ብንሸናነፍ ልክ አንሆንም። ያለፉ ታሪኮቻችን የጦርነት እና የኃይል መድረኮች ነበሩ። ኮሽ ባለ ቁጥር ጦር እየተማዘዝን ስንገልና ስንሞት ነበር። በዚህም እልፍ የወየቡ ታሪኮችን ከመጻፍ ጎን ለጎን ለዛሬ ጉስቁልና መነሻ የሚሆኑ ቁርሾዎችን ፈጥረናል።

> **አጉል መሻት ከሸነቆረው የዘረኝነትም ይሁን የጥላቻ ቀዳዳ መውጫችን ምክረ ሀሳብ ነው። በሀሳብ ካልተሸናነፍን በምንም ብንሸናነፍ ልክ አንሆንም። ያለፉ ታሪኮቻችን የጦርነት እና የኃይል መድረኮች ነበሩ**

ከሀሳብ ጎሎ በኃይል ለበረታ አእምሮ ገሎ ከመሞት በቀር ጀግንነት የለውም። ተነጋግረን በመግባባት ተነጋግሮ የሚግባባ ትውልድ እንፍጠር። ላለውም ሆነ ለሚመጣው ትውልድ በኩረ መነሻዎቹ እኛ ነንና ታርቀን እርቅን፣ ተፋቅረን ፍቅርን፣ አንድ ሆነን አንድነትን ልናስተምረው ይገባል።

ሀሳብ የሌላት ሀገር ማር የሌለው ቀፎ ናት። ቀፎ ማር እንዲሰጥ አበቦች ባሉበት፣ ለምለምና ለንቦች ምቹ በሆነ ቦታ ይሰቀላል። ይሄ ካልሆነ ግን ንቦች ወደቀፎው አይገቡም፣ ቀፎውም ማር አይዝም፤ በተስፋ ብቻ ማር መቁረጫ ቀን እንቆጥራለን። ልክ እንደቀፎው ሀገር ሰላምና ብልጽግና፣ አንድነትና ፍቅር እንዲኖራት የሀሳብ ሥልጣኔ፣ የእርቅና የምክክር ባሕል ያስፈልጋታል። አሁናዊው የሀገራችን ሁኔታ ከአበባ እንደራቀው ማር አልባ ቀፎ ነው። ቀፎው ማር እንዲይዝ የቦታ ለውጥ ያስፈልገዋል። ሀገራችን ሰላም እንድትሆን የምክክር መድረክ ያስፈልጋታል።

ትግላችን ከሌሎች ሀገርና ሕዝቦች ጋር ቢሆን ጥሩ ነበር። እኛ ግን የምንታገለው ከራሳችን ጋር ነው። እያወደምን ያለነው የራሳችንን ታሪክ ነው። እያበላሸን ያለነው የራሳችንን ትውልድ ነው። በእኛው እኛው እየተጎዳን ብዙ ዘመናትን ተሻግረናል። ሰው ከራሱ ጋር እንዴት ይጣላል? የሰሉ የከፋት አንደበቶቻችን ፍቅርን እንዲዘምሩ፣ ለመለያየት የበረቱ ምላሶቻችን ስለአንድነታችን ደጅ እንዲጠኑ ከፊታችን ያለውን ሀገራዊ ምክክር እንጠቀምበት።

ሕልሞቻችን መግባባትን ካለበሱ ከምኞት ባለፈ ፍሬ አይሰጡንም። በብሔር ደፈጣ የመጣ ንበት ረጅም ጎዳና ከድህነትም ሆነ ከኋላቀርነት አልታደገንም። የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል እንደሚባለው በጋራ ጉዳያችን ላይ ፉክክር ውስጥ የገባንበት ሁኔታ ነው የሚስተዋለው። የሚመጣው ካለው ካልተሻለ፣ ያለው ካለፈው ካልበረታ የተሻለ ነገር ማለማችን ፋይዳ አይኖረውም። በፉክክር ጉዟችን ካለውህ ባዷቸውን ያስቀመጥናቸው ብዙ ማድጋዎች አሉን። ሊያጠግቡንና ሊያረኩን የሚችሉ ታሪክና እሴቶቻችን ወዳጅነትን አጥተን ደብዝዘን አደብዝዘናቸዋል።

በሀሳብ ልውውጥ በሀሳብ የበረታ ትውልድ መሥራት ከየትኛውም ዓበይት ጉዳያችን ፊተኛው ነው። ለሁሉም ግፍ ያለፉትን ሀምሳ ዓመታት እናነሳለን። እኛም እኮ የዚህ ትውልድ አንድ አካል ሆነን እየኖርን ነው። አሁን ላለችው ኢትዮጵያና አሁን ላለው ትውልድ ምን እያደረግን ነው? ወቃሽ ከመሆን እና ያለፈውን ከመተቸት ውጪ ምን የሚያስመሰግን ሥራ ሠራን? የቆምነው እኮ በዛ ዘመን የፍቅርና የአብሮነት ክንድ ነው። የምንጠራው እኮ አባቶቻችን ባጸኑት የአንድነት ስም ነው። እንጂማ ምን ስም አለን? ከጥላቻና ከመገፋፋት ሌላ ምን ያተረፍነው ነገረ አለ?

የሄደው እንዳለ ሁሉ የሚመጣም ትውልድ አለ። ለመመስገንም ሆነ ለመተቸት ጊዜው የእኛ ነው። ያለፈውን የፖለቲካ ሥርዓት እንደኮነንን ሁሉ መጪው ትውልድ እኛ ባነወርነው ሀምሳ ዓመታት ላይ የእኛን ትውልድ ጨምሮ እንዳያስነውረን ዛሬን በጎ እንሥራ። ትናንሽ ቀዳዳዎቻችን ሰፊ እስኪሆኑ ሳንጠብቅ በቶሎ መድፈንን እንልመድ። አንዳንድ ንትርኮች ትላንት ላይ ተቋጭተው ቢሆን ዛሬ ላይ በዚህ ልክ አይበድሉንም ነበር። የዛሬ ትናንሽ መመላለሶች ነገ ላይ የበረቱ ሆነው ዋጋ እንዳያስከፍሉን ማሰቡም ተገቢ ነው።

ትውልዱ የፍቅር ውርስ ያስፈልገዋል። ወንድማማቾች በቀይ ምንጣፍ ላይ ተያይዘው ሲራመዱ እንዲያይና ለዛ ክብር ራሱን እንዲያዘጋጅ ምልክት እንስጠው። ከዛሬ አርቆ የተስፋ ነገን እንዲያይ የመነጋገር ውርስን እናውርሰው። በፖለቲካውም ሆነ በፖለቲከኞቻችን ስጋት የወደቀበት ትውልድ እየተፈጠረ ነው። ተስፋ እንጂ ስጋት ማንንም አጽንቶ አያውቅም። ክፍተቶቻችን በፍቅር ተሞልተው፣ በእርቅና በምክክር ታርቀው ጦርነትን እርም የሚል ትውልድ ዘርተን እናብቅል።

ያለፈውን ትተን መጪውን የምንቃኝበት በፍቅር ጀምሮ በፍቅር የሚያበቃ አዲስ ታሪክ ያስፈልገናል። የቂም በቀል ሳይሆን የወንድማማችነት ውርስ ነው የሚያስፈልገው። ሀገር ሰላምን ባነገቡ በላቁ ሀሳቦች ካልተማገረች የዘላቂነት ዋስትና አይኖራትም። ይሄ ጊዜ ከመቼውም በላይ ራሳችንን ከጦርነት ነፃ የምናወጣበት፣ የወንድማማቾች ግፊያ የሚያበቃበት ነው። ስለሀገራችን ሁሉንም በጎ መስዋዕት የምንከፍልበት ነው።

የምንገፋፋው ባልገባንና ባልተረዳንው ያለፈ ታሪክ እንደሆነ ግን ታውቃላችሁ? በሀገራችን ጥቂቶች የሚነዱት እልፍ መንጋ አለ። መንጋው ከኋላ ሆነው ለሚነዱት መጠቀሚያ ነው። እናም አልገባንም የምንለው በምክንያት ነው። ሳይገቡን ከምንጣላባቸው ይልቅ ገብተውን የሚያዋድዱን እልፍ የጋራ በረከቶች አሉን። ወደገቡንና የጋራችን ወደሆኑት ፀጋዎቻችን እስካልተመለስን ድረስ ባልገቡን ነገሮች ዋጋ መክፈላችን ይቀጥላል።

ትውልዱን በነገር መርዘን ጎራዴ የምንማዘዘው ምንም ባገባን መሆኑ የምንጊዜም አግራሞቴ ነው። ታሪክ ያዛነፋቸው እና እኛው ራሳችን ያዛነፍናቸው የመለያየት ቁርሾዎች ለማንም እንደማይጠቅሙ ከተረዳን ሰንበትበት ብለናል። እንዳረዳዳችን ግን ከማይጠቅመን የኩርፊያና የመለያየት መንፈስ ውስጥ ስንወጣ አንታይም። ዛሬም ድረስ በነዛ ባልገቡን ነገሮች ስር ቆመን ዋጋ ከፍለን ዋጋ የምናስከፍል ነን።

በሀገራችን ሰማይ ላይ የተስፋ ፀሐይ እንድንወጣ ምሥራቅ መሆን አለብን። ምሥራቅ በሌለበት ፀሐይ አትኖርም። ምሥራቅ ካለ ጀምበር አለች። ጀምበር ካለ ትንሳኤ አለ። በእርቅና በምክክር ለሀገራችን የፀሐይ መውጫ አድማስ ሆነን ትውልዱን የፍቅር ፀሐይ እናሙቀው የመጨረሻ መልዕክቴ ነው።

# ስፖርት




# የማረሚያ ቤቶች ቦክስ ክለብን ወደ ታሳቅነቱ የመመለስ ውጥን

ዓለማየሁ ግዛው

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ስፖርት ክለብ ኢትዮጵያን በኦሊምፒክና በሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮች መወከል የቻሉ ቦክሰኞችን በማፍራት ትልቅ ስም ካላቸው ክለቦች ግንባር ቀደሙ ነው። ክለቡ በቦክስ ስፖርት ስመ ገናና እና ቀደምት ቢሆንም ባለፉት ጥቂት ዓመታት ግን እንቅስቃሴው ተቀዛቅዟል። የክለቡ ውጤት ከነበረበት እንዲንሸራተት ምክንያት የሆኑትም የልምምድ ቦታ ማጣትና የገንዘብ ችግሮች ናቸው። ችግሩን በመቅረፍ ክለቡን ውጤታማ ለማድረግና ወደ ቀደመ ዝናው ለመመለስም ግን በዚህ ወቅት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ክለቡ በኅዳር ወር ይጀመራል ተብሎ በሚጠበቀው የኢትዮጵያ ቦክስ ክለቦች ሻምፒዮና ጠንካራ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብም ዝግጅቱን ከጀመረ ከሁለት ወራት በላይ አስቆጥሯል። ክለቡ የመለማመጃ ቦታ ችግር ያለበት ቢሆንም በጎ ሰዎች ባደረጉት ድጋፍ አብነት አከባቢ በሚገኘው ወወክማ ልምምዱን አጠናክሮ ቀጥሏል። ሁሉንም የቦክስ ክብደት ሚዛኖችን የያዘ ዝግጅትን በማድረግም የውድድሩን መጀመር ብቻ በመጠበቅ ላይ እንደሚገኝም የክለቡ አባላት ገልጸዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ቦክስ ፌዴሬሽን በሚያዘጋጀው ሻምፒዮና አጃቢ ሳይሆኑ ተፎካካሪ ሆኖ ለመቅረብ ከፍተኛ ዝግጅት እያደረጉ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

ለማንሰራራት ጥረት እያደረገ ያለው ይህ ክለቡ፤ ኢትዮጵያ በቦክስ ስፖርት በዓለም መድረክ እንድትወከል የድርሻውን አበርክቷል። ሰለሞን ታደሰ፣ ዮሐንስ ሽፈራው፣ ሲሳይ አበበ፣ ተስፋ ወርቅ፣ ኮማንደር ፀጋሥላሴ አረጋይ እና ሌሎች ስማቸው ያልተጠቀሰ ኮከብ ቡጢኞችን ያበረከተ ታሪካዊ ክለብ ነው። በ1970ቹ እና 80ዎቹ የነበሩት ድንቅና ብቃት ያላቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ቦክሰኞች ውስጥ አብዛኞቹ የፌደራል ማረሚያ ቤቶች እንደሆኑ ይታወቃል።



አንጋፋውን የቦክስ ክለብ ወደ ተፎካካሪነት ለመመለስ በርካታ ጥረቶች ተደርገዋል፣

የኢትዮጵያን ባንዲራ በዓለም አደባባይ እንዲውለበለብ ከፍተኛ አሻራቸውን ያስቀመጡ ውድ ስፖርተኞችን ያፈራ ታላቅ ክለብ ነው ቢባልም ማጋነን አይሆንም። ነገር ግን እንደቀድሞ ውጤታማ ቦክሰኞችን የማፍራትና በብዛት ለብሔራዊ ቡድን የማስመረጥ ድርሻው ከቀነሰ ሰነባብቷል፡፡

የማረሚያ ቤት ቦክስ ክለብ ቡድን መሪ ኮማንደር ፀጋሥላሴ አረጋይ (ኮሩ) ስፖርት በተለይ ቦክስ ከገንዘብ፣ ከምግብ፣ ከልምምድና ከመወዳደሪያ ስፍራ አንጻር አቅምን እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ። የልምምድና የመወዳደርያ ቦታና ቁሳቁስ ለማግኘት እንዲሁም የገንዘብ አቅምን ለመፍጠርም እንቅስቃሴዎች ተጀምረዋል። ቀድሞ ማረሚያ ቤቶች የሚጠቀምበት መዝናኛ ክበብ ለሌላ ጉዳይ መዋሉን ተከትሎ ምትክ ቦታ ቦሌ ኢምፔሪያል አካባቢ እንደተሰጣቸውና እሱን በማሠራት ለልምምድ እንዲውል እንዲሁም በኪራይ ለክለቡ የገቢ ምንጭም ይውላልም ብለዋል። ቀደም ብሎ ቦታው በመወሰዱ ከዛ የሚገኝ ገቢ በመቅረቱ ላለፉት ስድስት ዓመታት ገደማ ክለቡ ችግር ውስጥ በመግባቱ ተቋሙ ለቦክስ ባለው ክብር በመዋጮ ክለቡ እንዲቀጥል ማድረጉን ይጠቅሳሉ። ይህም የሆነው ማረሚያ ቤት ቦክስ ክለብ ታሪካዊ ክለብ በዚህ ጊዜ ፈረሰ ብሎ በትውልድ እንዳይወቀስ ጥረት በሚያደርጉ አካላት እስከ አሁን ቆይቷል። ስፖርቱ ገንዘብ እንደመጠየቁ ማረሚያ ቤት ያፈራቸውና ዓለም አቀፍ ዕውቅና ያላቸው እንዲሁም ኦሊምፒክ ድረስ የተወዳደሩ ቦክሰኞችን በማስተባበር የገቢ ማሰባሰቢያ ዘመቻም ይደረጋል።

በተጨማሪም በሻምፒዮውናው ተጠናክሮ ለመቅረብ አሠልጣኞች እና ስፖርተኞች በትጋት እየሠሩ እንደሆነም ቡድን መሪው ይጠቁማሉ። ተፎካካሪ ለመሆንም አዳዲስ ቦክሰኞች ቡድኑን እንደተቀላቀሉና የመለማመጃ ቦታ ማመቻቸትን ጨምሮ አስፈላጊ ድጋፍ ተደርጓል። ለዚህም የቡድኑ መነቃቃት እና ልምድ ባላቸው ኢንስትራክተሮች መሠልጠኑ የሥነልቦና እና የአካል ጥንካሬን ለቡድኑ የሚሰጥ በመሆኑ ውጤት እንዲጠብቁ አድርጓል። በቅርብ ጊዜ ለተከታታይ የውድድር ዓመታት በውጤታማነት ለመቀጠል ሁኔታዎችን እያመቻቹ መሆኑንም ያምናሉ። የክለቡን ውጤታማነት ለማስቀጠል ዋነኛ ጉዳይ የሆነውን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍም የገቢ ምንጫቸውን በማስፋት መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ተጠናክሮ የሚሠራም ይሆናል። ክለቡ ልምድ ባላቸው፣ በወጣቶችና ታዳጊዎች በመዋቀሩ ከክለቡ አልፎ ለሀገር መብቃት የሚችሉ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የፌደራል ማረሚያ ቤት ስፖርት ክለብ በ1975 ዓም በወቅቱ በማረሚያ ቤት ዋና አስተዳደር በነበሩት በኮሎኔል አበራ አያና አማካኝነት ሊመሠረት ችሏል። ክለቡ ከተመሠረተ አንስቶ የሀገርን ባንዲራ ከፍ ማድረግ የቻሉ በርካታ ስፖርተኞችን ማበርከት ችሏል። አትሌቶች፣ ቦክሰኞች፣ የእጅ ኳስ እና የቮሊቦል ተጫዋቾች የወጡበት አንጋፋና ቀደምት የስፖርት ክለብም ነው። ክለቡ በኦሊምፒክና በዓለም ሻምፒዮና መድረኮችም ኢትዮጵያን ማስጠራት የቻሉ ውጤታማ ስፖርተኞችን ያፈራ ታላቅ የስፖርት ክለብ ነው። ከቦክሱ ባሻገር በአትሌቲክስ ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ፣ ስለሺ ስህን፣ ጥሩነሽ ዲባባ፣ ፋጡማ ሮባ፣ ቁጥሬ ዱለቻ እና አንጋፋውን አሠልጣኝ ኮሚሽነር ሁሴን ሽቦን የመሳሰሉ ፈርጦችንም አበርክቷል፡፡

## ሐረሪ ክልል

በአቶ ከሳቴ አርአያ ብርሐን ስም ተመዝግቦ ስለሚገኝ የሰሌዳ ቁጥር 01-03176 ሐረ የሆነ ተሽከርካሪ ሊብሬ ጠፋብኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡
በዚሁ መሠረት ይህን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት ትራንስፖርት ጽ/ቤት**

## ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል

በከሳሽ ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ኢፋ ሽፈራ ኢትቻ መካከል ስላለው ከባድ ሰው መግደል ወንጀል ክስ ጉዳይ አስመልክቶ ተከሳሹ በቀበሌው የለለ መሆኑን ፖሊስ በማረጋገጫ ያቀረበ ስለሆነ ተከሳሹ በቀጣይ ቀጠሮ አሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት ቀርበው እንድከራከር ፤የማያቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌበት የሚታይ መሆኑን አውቀው በቀጣይ ቀነ ቀጠሮ ለጥቅምት 26 ቀን 2016 ዓ/ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እንዲቀርብ የአሶሳ ከተማ ከፍ/ፍ/ ቤት የወንጀል ችሎት አዟል፡፡

**በቤ/ጉ/ክ/መንግስት የአሶሳ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወንጀል ችሎት**

## ኦሮሚያ ክልል

በከሳሽ አቶ በቀለ ወ/ሰማያት እና 1ኛ ተከሳሽ በክሪ ሀይሩ፣ 2ኛ አቶ ቤለሞ ዴዴ መካከል ያለውን የፍትሐብሔር ክርክር አስመልክቶ ተከሳሾች መከሰሳቸውን አውቀው ለቀጠሮ ቀን 30/02/2016 4፡00 ሰዓት ላይ እንዲቀርቡ የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ጉዳይ ችሎት**

በአመልካች አበራ ከበደ እና በተጠሪ ፈታሌ ጎሳ መካከል ስላለው የባልና ሚስት ክርክር ፍ/ቤቱ በ13/02/2016 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተከሳሽ ለ27/02/2016 ዓ.ም. በ4፡15 ሰዓት እንዲቀርቡ የገፈርሳ ጉጂ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት አዟል፡፡

**በገፈርሳ ጉጂ ክፍለ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ችሎት ቡድን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሾች እነ አቶ ሀብታም ጌትነት እና በተከሳሾች እነ 1ኛ/ አቶ ግዛቸው ተፈራ መካከል ስላለው የፍታብሔር ክርክር ጉዳይ 1ኛ ተከሳሽ አቶ ግዛቸው ተፈራ ፣ 3ኛ ተከሳሽ አቶ ታዴ መኬ ለ30/2/2016 ዓ/ም 4፡00 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ እንዲቀርቡ ሲል የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ን/ስ/ላ ምድብ ችሎት አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የንፋስ ስልክ ላፍቶ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች እነ ወ/ሮ ማንያህልሻል እንዳለ አየለ እና
በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ተሾመ ተስፋዬ ሣ/ማርያም
መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 19ኛ ሁከት ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ23/02/2016 ዓ.ም. በ4፡20 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች አቶ ወንድወሰን መኮንን እና
በተከሳሽ/ተጠሪ ወ/ሮ ምስክር አስራት
መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ03/03/2016 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም በሬቻ ፈይሳ ተክሉ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-A12739 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB8MN888797 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*210507041047* የሊብሬ ቁጥር 0233868 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር / ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 14/2/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**

ከሳሽ አቶ ሚኒሊክ አየለ መስፍን እና ተከሳሽ አቶ ቶሌራ ቦርጋ ገመቹ በጥቅምት 27/2016ዓ/ም 4:30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አዲስ አበባ ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል።

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የየካ ምድብ ችሎት**

በፍ/ባለመብት አቶ ኤፍሬም ተስፋዬ እና
በፍ/ባለዕዳ ወ/ሮ ወርቅነሽ ከበደ
መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃ/ቃ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ23/02/2016 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ መድህን ተስፋይ ግደይ እና
በተከሳሽ/በተጠሪ አቶ ለምለም በርሔ ንጉሴ
መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 2ኛ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ26/02/2016 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት መልስ ለመቀባበል በ27/02/2016 ዓ.ም. በ4፡30 ሰዓት ለስምምነት በ28/02/2016 ዓ.ም. 4፡30 ሰዓት ክስ ለመስማት ላሉት ቀጠሮዎች እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም ትዕግስት ክፍሌ አየለ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-01103 የተሽከርካሪው አይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር 381003.14-387542 ሞዴል 1213AK የሞተር ቁጥር 353944-10489282 የሊብሬ ቁጥር 313669/160839 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 15/2/2016 አመልክተዋል፡፡
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የኮልፌ ቀራንዮ ቅ/ጽ/ቤት**